# ፅብረቃ ተኮር መጻፍ ዘዴ የመፃፍ ችሎታን ለማጎልበት ያለው አስተዋፅኦ፤ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን በወረጅሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡ ፡

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናታዊ ጽሑፍ የቀረበ ትልመ ጥናት


በ

መልካሙ ኤባ…………………….. WU 1008547

አማካሪ

ታሪኩ ለገሰ (ዶ/ር)

በወለጋ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናትና ጋዜጠኝነት ተቋም

በቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የአማርኛ ትምህርት ፕሮግራ



ጥር 2014

ነቀምቴ


ወለጋ ዩኒቨርስቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ፅብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ያለው አስተዋፅኦ፤ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን በወረ ጅሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳርነት ፡፡

በመልካሙ ኤባ

WU1008547

ታሪኩ ለገሰ (ዶ/ር)

ወለጋ ዩኒቨርስቲ

2014 ዓ.ም

ወለጋ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

**በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታን ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ  በሚል ርዕስ በመልካሙ ኤባ  በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበው ጥናት በውጭና በውስጥ ፈታኞች ተገምግሞ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡**

**ፈታኞች ቦርድ**

| ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| 1____________________ | _______________ | _______________ |
| 2____________________ | _______________ | _______________ |
| 3____________________ | _______________ | _______________ |

## ማረጋገጫ

**‹‹ፅብረቃ ተኮር መጻፍ ዘዴ የመፃፍ ችሎታን ለማጎልበት ያለው አስተዋፅኦ፤ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን በወረጅሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት››** በሚል ርዕስ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ፣የቋንቋዎች ጥናትና

ጋዜጠኝነት ተቋም፣ የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል በተዘጋጀ አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና፣ የተጠቀምኩባቸው ዲርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና ወለጋ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡ በመልካሙ ኤባ

ፊርማ________________________

ቀን____________________________

**ምስጋና**

ጥናቱ ተጀምሮ እንዲጠናቀቅ ፍቃዱ ለሆነ ለጅማሬም ለፍጻሜም አምላክ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ዛሬም ዘወትርም የተመሰገነ ይሁን፡፡

የጥናቱ ርዕስ ከማስተካከል ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ያለምንም መሰላቸት ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው በተደጋጋሚ በማየትና እጅግ ፈጥኖ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት እውቀታቸውን በማካፈል የተዛባውን ስራ እያቀኑ ጥናቱ ከዳር እንዲደስ ትልቁን ድርሻ ለተወጡ ምሳሌነታቸውን ሁሌም ለማልረሳው ለአማካሪዬ ዶ/ር ታሪኩ ለገሰ እና ዶ/ር መዓዛ ደጀኔ ምስጋናዬ ወሰን የለውም፡፡

ውድ ባለቤቴ ወርቅነሽ ቶቶባ ሙሉ ጊዜዋን ለጥናቱ ስራ ስጠቀም ላሳየሽኝ ከልብ የመነጨ ትዕግስትና ላደረግሽኝ ማበረታቻ ሁሉ ምስጋየ ከልብ የመነጨ ነው፡

ለጥናቱ አገልግሎት የሚውል ላፕቶፕ በመስጠት የወረ ጅሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ ደሳለኝ ገነቲ እና በጽሕፈትና በእዲት ከጎኔ ሆኖ ለተባበረኝ ጓደኛዬ መ/ር ምስጋኑ እጣናን ምስጋናዬ ከልብ ነዉ፡ ፡

እንዲሁም ጥናቱን ሲያካሄድ ከጎኔ ሆኖ በበጀትና በምክር ያልተለዩኝ ዉድ ወንድሞቼ ታማነ ኤባ ኦፍካላ ኤባ ዓለሙ ኤባ እና አባቴ አቶ ኤባ ታስሳ እና እናቴ ወ/ሮ ክብቱ ተርፋ እወዳችኋለሁ ኑሩልኝ፡ ፡

የይዘት ማውጫ


የዘት ገጸ

ማረጋገጫ ........ iv

ምስጋናv

አህፅሮተ ጥናት ........ vii

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ ........ 1

1.1.የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱመነሻችግር........7

1.3 የጥናቱ ዓላማ ........ 12

1.4 የጥናቱአስፈላጊነት ........ 12

1.5 የጥናቱወሰን ........ 12

1.6 የጥናቱ ውስንነት ........ 13

1.7 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳብ አጠቃቀም ብያኔ ........ 13

2.1 በጽብረቃ ተኮር ናየመጻፍ ችሎታ ትስስር ........ 15
ምዕራፍሶስት፤የአጠናንዘዴ........ 20
3.1 የጥናቱ ተሳታፊዎች........ 20
3.2 የመረጃመሰብሰቢያመሳሪያዎች........ 21
3.3 የማስተማሪያመሳሪያዎች........ 22
3.4. የአጠናንሂደት........ 23
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ........ 24
ምዕራፍ አራት፣ የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........ 25
4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና........ 25
4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 31
ምዕራፍአምስት፤ማጠቃለያ መደምደሚያና መፍተሄ ሀሳቦች ........ 34
5፤1 ማጠቃለያ........ 34
5.2.መደምደሚያ........ 36
5.3 መፍትሔ........ 36
ዋቢዎች ........ 38
አባሪዎች ........ 41

**አህፅሮተ ጥናት**

የጥናቱ አቢይ ዓላማ በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለውን አስተዋፅኦ መመርመር ነበር፡፡ የጥናቱ አካባቢ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን በለታ ስቡ ወረዳ በወረ ጅሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ነዉ፡፡ትምህርትቤቱ የተመረጠው በዓላማ ተኮር የእጣ ናሙና ነው፡፡

በዚሁ ትምህርት ቤት በ2014 ዓ.ም በ9ኛ A እና 9ኛB ክፍል የሚማሩ 50 ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ ጥናቱ ፈትነታዊ (የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረ)ነው፡፡ለመረጃ መሰብሰቢያ ፈተናዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡የቅድመ ትምህርት የመፃፍ ፈተና የተሳታፍዎችን ዳራዊ እውቀት ለመለካትና የጥናቱን ተሳታፍዎች ለመምረጥ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ለስድስት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ቀን ለጥናቱ ተሳታፍዎች ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ተሳታፍዎች በተሰጠው ትምህርት ያመጡትን ለውጥ ለመለካት በድህረ ትምህርት ፈተና መረጃ ተሰብስቧል፡፡መረጃውም በገላጭ ስታትስቲክስ (በአማካይና በመደበኛ ልይይት እና በድምዳሜያዊ (ነጠላ ልይይት) ተተንትኗል፡፡በውጤት ትንተናውም በቅድመና ድህረትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት (p,< 0.05) ታይቷል፡፡ይህም የተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ መሻሻሉን

አሳይቷል፡፡በተመሳሳይ የጥናቱን ተሳታፍዎች የመፃፍ ችሎታ ለመፈተሽ የቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ እና ትምህርቱ ከተሰጠ ቦሃላ የመጣውን ለውጥ ለማወቅ የድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታን በጥናቱ ተሳታፍዎች ተሞልቷል፡፡በውጤቱም በቅድመና ድህረትምህርት የመፃፍ ችሎታ አማካይ ውጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ($p<0.05$) ልዩነት ታይቷል፡፡ይህም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታን መማር የመፃፍ ችሎታ በመነሳሳት ረገድ አዎንታዊ ሚና እንዳለው አመላክቷል፡፡በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርት ሂደት የጽብረቃተኮር መፃፍ የመጻፍ ችሎታን ለመመርመር የተማሪዎች የማስተማሪያ መሳሪያ በመረጃ ምንጭነት አገልግሎዋል፡፡ይህም ተሳታፍዎቹ በጥናቱ መነሻ ስለፅብረቃተኮር መፃፍ ከነበራቸው ግንዛቤ አንፃር የፅብረቃተኮር መፃፍ የመጻፍ ችሎታን ግንዛቤያቸው እንደተሻሻለ አመላክቷል፡፡ በውጤቱ መሰረት በፅብረቃተኮር መፃፍ መፃፍን ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የጎላ ሚና ስላለው በመፍትሄነት ተጠቁሟል፡፡

## ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

### 1.1.የጥናቱ ዳራ

ጽብረቃ የመማር ሂደትና የመማር ትርጉምን አስተሳስሮ የሚያሳይ የታቀደ አእምሮአዊ ተግባር ነው፡፡ ጽብረቃ ችግርፈቺ ተግባር ሲሆን ማሕቀፉም ተማሪዎች ጥልቅ እሳቤ ለማዳበር እንዲችሉ በርካታ አጋጣሚዎችን ይፈጥራል (Andrusyszym 1997) ፡፡ እንደ Goldberg.N (1993) ገለፃ በጽብረቃተኮር መጻፍ የተነቃቃ የትምህርት ሂደትን ለመገንዘብና የመፃፍ ችሎታን ለማሻሻል ያስችላል፡፡ በRachilong (1997) የተጠቀሱት Cirowun እና ሌሎች (1986)ን እንደገለጹት መፃፍ የሀሳብ ክስተት ነው፡፡Hampe.N (2013) እንደሚያብራሩት ደግሞ ጽብረቃተኮር መጻፍ የጽብረቃ እሳቤ ማስረጃ ነው፡፡ በMoon.J (2004),በJuli እና chu (2012) የተጠቀሱትን Taylor እና Waity (2000) የጽብረቃተኮር መጻፍ ቀዳሚ ትኩረት የንድፈ ሀሳብ አተገባበር ሂደትን ማሳወቅ ነው፡፡

እንደ Ramseden.P(1992),Watten.P,Collings,Moon.J (2001),ገለጻ መማር ጽብረቃን ይፈልጋል፡፡ ጽብረቃ ተኮር መጻፍን ለመተግበር ደግሞ ግንዛቤያዊ ሂደት ነው፡፡ እ.አ.አ. ከ1980ዎቹ ወዲህ የጽብረቃ ተኮር መጻፍ እሳቤ በጣም ቴክኒካልና ስልታዊ እይታ ይዞ በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ እንደ Goldberg.N (1993) አገላለጽ የጽብረቃ ተኮር መጻፍ ተግባር አዲስ ቢመስልም የመጀመሪያው በትንሹ ተቀይሮ በአዲስ ተተካ እንጂ ጽብረቃ ተኮር መጻፍ ረጅም ታሪካዊ ዳራ ያለው ነው፡፡ በጽብረቃ ተኮር መጻፍ መማርና የመፃፍ ችሎታ ትግበራ መነሻው በስርዐት የተዋቀረ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ በርካታ ጥናቶች ለጽብረቃ ተኮር መጻፍ እሳቤ የተለያዩና ተመሳሳይነት ያለቸው ጭብጦችን ይሰጣሉ፡፡ የጽብረቃ ተኮር መጻፍ ትግበራ መነሻው ብዙ ክፍለ ዘመን ወደ ኋላ ተጉዞ ከቀደምት ፈላስፋዎች ይደርሳል፡፡ ጉልህ አስተዋጽኦ ካበረከቱት ለምሳሌ፤ John Dewey, (1933;1938) ቀዳሚ ሲሆን በብዙ ተመራማሪዎች የሚጠቀሱና በሌሎች ተመራማሪዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳደሩ ናቸው (Ramsden.p1992, Goldeberg 1993)፡፡

Ramsden.P (1992) እና Goldeberg.N (1993 )እንደሚያብራሩት Johndewey (1993) ለበርካታ ቀደምት ምዕራባውያንና ምስራቃውያን ፈላስፎች የትምህርት ባለሙያዎች ቡድሐ፣ፕሌቶና ሌዎ-ቲዙን ጨምሮ በ20ኛው ክፍለ ዘመን በትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍን መጠቀም ያሳዩና በሌሎች ተመራማሪዎች ዘንድ ተጽዕኖ የፈጠሩ ሰው ናቸው ፡፡ በተጨማሪም Linda.D (2001),Goldberg (1993) እንደሚብራሩት Findiler (2003),Rojers (2002), colten (1991), Zeichner and laston (1996) በJohndewey (1933) ስራ ላይ ተመስርተው ለጽብረቃተኮር ትግበራ ሞደል በርካታ አስተዋጽኦ አበርክቶዋል፡፡

Ramseden.P (1992), Goldberg.N (1993) እንደሚያብራሩት ጽብረቃተኮር መጻፍ በማህበራዊ መስተጋብር እሴት ሞራል በመገንባትና ስነምግባራዊ ግንዛቤ በማህበረሰብ ላይ በመፍጠር ባህልንና ማንነትን ያስገነዝባል፡፡ፅብረቃተኮር መጻፍ በተለያየ መንገድና በተለያየ ዓላማ እንዲሁም በተለያየ ውጤት ይከሰታል፡፡በርካታ ጥናቶች እንደሚገልጹት ቀዳሚው Johndewey and ዘመነኛው Donald Schon የፅብረቃ ግንዛቤን ለማህበረሰብ በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

የጽብረቃተኮር መጻፍ እሳቤና የፅብረቃተኮር መጻፍ ትግበራ ለበርካታ አስርት አመታት ብቻ ሳይሆን ለክፍለ ዘመናት ታወቂ ፈላስፎች ንድፈ ሀሳባውያን፤መምህራን ባለሙያዎች የተሳተፉበት በጥንቃቄ የተዋቀረ ንድፈ ሀሳብና በጥናትና ምርምር የተተገበረ እውቀት ነው Goldberg.N (1993)፡፡ ለዚህ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው የተለያየ ፍልስፍናና የተለያየ ትኩረት የተለያየ ንድፈ ሀሳብ ይከተሉ የነበሩ አካላት ለፅብረቃ እሳቤና ለፅብረቃ ትግበራ የነበራቸው ትኩረት ነው፡፡ለምሳሌ፤Buddha (624 Bc),SUzki (1982),Nihati han (1993)ን ጠቅሰው Goldberg.N (1993) እንዳብራሩት Buddha አብይ ትኩረቱ የተለዋዋጭነትን እውቅና መፍጠርና ትምህርት ሁልጊዜም ጊዜያዊ መሆኑን ለመስገንዘብ ነው፡፡ በBuddhism (624) ቀጥተኛ ልምድ እውነት ነው፡፡የትምህርት ባለሙያዎች ምርምር አያስፈልግም ምክንያቱም የነባራዊው አለም አኗኗር እውነትን ለመመርመር የሚያገለግል መሳሪያ ነው፡፡ Guldisten እና kerenfeld (1987፣87) ጠቅሰው Goldeberg.N (1993) እንደገለፁት በጥልቀት ማዳመጥና ጠንካራ ስሜት የBuddha አንዱ ትምህርት ነው፡፡

በአንፃሩ Robsen (1993) እና Goldberg.N (1993) እንደሚስማሙበት ደግሞ ከ471-469 አ.አ.አካባብ ባለው ውስጥ እንደተወለው የሚገመተው Socrates እንደገለፁት ምርምር የሌለው ህይወት ዋጋ የለውም፡፡ከዚህ ገለፃ በስተጀርባ ልምድ የሚተረጎምበት ክፍል አለ፡፡Socrates ስነዘዴ የትምህርት ንድፈ ሀሳብ መሰረት በእምነት በዲያለክት አቀራረብ ጥያቄና መልስ ላይ የተመሰረተን ግብ ቀጣይነት ያለው እሳቤ ቀጣይነት ያለው ተግባር እንደግብ ይሆናል፡፡ከላይ የተዘረዘሩት ሁለት የተቃረኑ እሳቤዎች ውስጥ የጽብረቃተኮር ትግበራ በንድፈ ሀሳብና በጥናት ምርምር ተተገብሯል፡፡

እንደ Goldberg.N (1993) ማብራሪያ Johndewey (1933፤1938),ከሚያተኩሩባቸው ነጥቦች ጥቂቶቹ የትምህርት ግቡ (እሳቤው) የትምህርት ባለሙያዎችን፤ ማህበረሰብን ማበረታታት፤ የእያንዳንዱን ሞራል ስነምግባር ማሳደግና ጠንካራና ፍትሃዊ ማህብረሰብ መፍጠር ነው፡፡ማህበረሰቡ ተገቢና እውነተኛ የችግሮችን ገጽታ እንዴት ያስባቸዋል/ይረዳቸዋል?ብሎ ይመረመራል፡፡በጽብረቃተኮር መጻፍ የመማር ሂደት ቀጣይነት ያለው የመፃፍ ችሎታን ለማዳበር ነዉ፡፡ይህ ልምድ በግለሰቡና በተገኘበት አውድ መካከል ያለውን መስተጋብር ማብራራትና በቀጣይነቱ የሚከተለውን ትርጉም መገንዘብ ትኩረቱ ነው፡፡የጽብረቃተኮር መጻፍ እሳቤ ስልታዊ ሂደት የመፃፍ ችሎታ ልምድን ማብራራት ከእውቀት የሚነሱ ጥያቄዎችን በጽሁፍ ምላሽ መስጠት መላምት መገንባት እነዚህ በሙሉ መነሻቸው ከግምት የሚገባው ከውጫዊው አካልና መላምት ከተወሰነለት ተግባር እውቀት የሚወስድ ነው የሚሉት ናቸው (Goldberge.N 1993)፡፡

Maksvan,Manen (1977) ን ጠቅሰው Goldberg.N,(1993) እንደሚያብራሩት ሶስት የተለያዩ የጽብረቃተኮር መጻፍ ደረጃዎችን የተለያየ አላማ ተጠቅመው ይተነተናሉ፡፡ እነሱም፤አንደኛ ቴክኒካል ጽብረቃተኮር መጻፍ ችሎታን፤ብልሐትንና ስነዘዴን ቀደም ከተወሰነው አላማ አንፃር ለመመርመር ነው፡፡ቴክኒኩ የተገበረ አላማው ግብ ይመታል፡፡ ሁለተኛ ተግባራዊ ጽብረቃተኮር መጻፍ የታሰበውን ስነዘዴ ከተጠቀመ ከግቡ ይደርሳል በሚለው ሀሳብ የሚያተኩሩበት ሲሆንየተማሪዎችን ውጤታማነት እንደገና ዓላማውን ይመረመራል፡፡ሶስተኛ ጥልቅ ጽብረቃተኮር መጻፍ ስለሞራል ስነምግባርና ተቀባይነት ባላቸው ተግባራት ላይ ያተኩራል፡፡

Kenez,zeichner and Danililston (1981),kenez zeichner (1993)ን ጠቅሰው Goldberg.N (1993),Finlay.L (2008) Andrusyszym.MA, Davi.L (1997) Lukas (2012) Boman.J (2014) እንደሚያብራሩት ጥልቅ ጽብረቃተኮር መጻፍ ለትምህርት አስፈላጊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ጥልቅ ጽብረቃተኮር መጻፍ እንዴት ለትምህርት ስራ ይውላል? የሚለውን የትምህርት ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች ትኩረት ሰጥተው እንዴት መመርመርና በት/ቤቶች ማስፋፋት እንደለባቸው ከመስራታቸው በተጨማሪ እሳቤው በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው የድርሻቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ሆኖም ግን የመምህራን ጽብረቃተኮር መጻፍ ለትምህርት በጣም አስፈላጊ ነው የሚለው እሳቤ ተግዳሮት ገጥሞት ነበር፡፡
ምክንያቱም የመምህራን ጽብረቃተኮር መጻፍ ለተማሪዎች አስተማማኝና ተገቢ የመፃፍ ችሎታ እውቀት የሚሆን የጽብረቃ ትግበራው ወቅታዊ ሲሆን ነው፡፡
Donald Schon (1983,1987)ን ጠቅሰው Goldnberg.N (1993),Hampe.N (2013) እንደሚገለፁት የSchon እሳቤ "ሙያዊ እውቀትን መተቸት ነው፡፡" ሙያዊ እውቀትና እውቀቱን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስፈልገው ችሎታ መካከል ክፍተት ለማሳየት ነው፡፡
በተጨማሪም የSchon አብይ ትኩረት ከልምድ ትክክለኛ እውቀት ማግኘትና ትግበራውን ማደራጀት ላይ ነው፡፡ መምህሩ እውቀትን ከልምድ ሲያገናኝና እንደገና ሲያዋቅር እውቀቱን ለተማሪዎች ሲተነተን ውስብስብ አጣራጣርና ወሰን አልባ አባባሎች ሊካተቱ ስለሚችሉ የጽብረቃተኮር መጻፍ አይነቶችም በተግባር ላይና ከተግባር በኋላ በሚል በሁለት ይካፈላሉ፡፡cliwon and Todinem(1991)በተጨማሪ Donald Schonን የጽብረቃተኮር መጻፍ አይነቶች መነሻ በማድረግ ከተግባር በፍት ጽብረቃተኮር መጻፍን አፍልቀዋል፡፡እንደ Goldenberg.N (1993) ማብራሪያ የጽብረቃተኮር መጻፍ ትግበራን ለማከናወን የሚያግዙ አራት ተግባራትን የመፈጸም ሀሳብ ያፈለቁ Davidsimaz (1989) ሲሆኑ የጽብረቃተኮር መጻፍ እያንዳንዱን ተግባር ለመፈጸም የሚመራ ጥያቄ አካተዋል፡፡እነሱም ምን እሰራለሁ? ምን ማለት ነው? እንዴት ለስበውና ልተገብረው ቻልኩ ? እንዴት በተለያየ ሁኔታ ልተገብረው ቻልኩ ? የሚሉት ናቸው፡፡

Karen Osterman and Robert coticamp (1993, 2004) ከመማር ማስተማሩ ሂደት ባሻገር በጽብረቃ ተኮር መጻፍ ትምህርት አውዱ እንዴት በባህል ይቃኝ? የሚል እሳቤ አላቸው፡፡ የተማሪዎችን ነፃነት በማይገፋ መልኩ ንድፈ ሀሳብ ምርምርን መሠረት አድርጎ እሳቤውን ተግባሩ የሚዋሐድበት ሂደት እንዴት ባህልዊ አውድ ይኑረው? ተማሪዎች ባህላዊ አውዱን እንዲገነዘቡት ምን ማድረግ ይቻላል? በሚሉት ጉዳዮች ላይ ያተኩራል (Goldberg N 1993)፡፡

Sparkes, Langer and cliton (1994) በጽብረቃተኮር መጻፍ ትግበራ ሂደት እውቀት ግንባታ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ጉዳዮችን ለይተዋል፡፡ እነሱም፡የአዲስ ልምድ ምርጫ እውቀት ሙያዊ እውቀት ስሜት ትምህርቱ የሚገኝበት አካባብና ግላዊ ባህርይን ማካተት ናቸው፡፡በተጨማሪም ጽብረቃተኮር መጻፍ ዙርመጥ ሂደት እንዳለው ማሕቀፉ በተሳታፊዎች ጽብረቃተኮር መጻፍ እንደሚያዳብርና ደረጃዎች እንዳሉት አስረድተዋል፡፡የሂደቱ ደረጃዎች ከተግባሩ መረጃ በመሰብሰብ ከበርካታ ተላውጦዎች አንፃር መረጃ በመተንተን መላምት በመንደፍ በትግበራው መላምቱን ለመፈተሽ ናቸው (Goldberg.N1993)፡፡

LindaValli (1997) ን ጠቅሰው Goldberg.N (1993) እንደሚያብራሩት ጽብረቃተኮር መጻፍ በተለያየ ቴክኒካል ጽብረቃተኮር መጻፍ፤ጽብረቃተኮር መጻፍ ተግባር ላይ፤ከተግባር ቦኋላ የታቀደ ጽብረቃተኮር መጻፍ፤ግላዊ ጽብረቃተኮር መጻፍ፤ጥልቅ ጽብረቃተኮር መጻፍ የሚሉ ክፍሎች አሉት፡፡ ቴክኒካል ጽብረቃተኮር መጻፍ መሠረቱ ምርምር ሲሆን አጠቃላይ ትምህርት ላይ የሚያተኩር መምራትን መለማመድ ነው፡፡ጽብረቃተኮር መጻፍ ተግባር ላይና ጽብረቃተኮር መጻፍ ተግባር ቦኋላ ደግሞ በአውድ ላይ ተመስርቶ ውሳኔ የሚሠጥ ነው፡፡

እንዲሁም የታቀደ ጽብረቃተኮር መጻፍ ትኩረቱ የመፃፍ ችሎታን ከተግባራዊነት ጋር የሚያያይዝበትን ፈርጀብዙ ብልሐት መፈለግ ሲሆን የታቀደ ጽብረቃተኮር መጻፍ እሳቤዎችን የተለያዩ ግንዛቤዎችን የምርምር ውጤቶችን በመገንዘብ ላይ ይሳተፋሉ፡፡ግላዊ ጽብረቃተኮር መጻፍ በአንድ ግላዊ ዕድገት ላይ በተማሪውና በተተኳሪ የመፃፍ ትምህርቱ አመለካከቱ ላይ በተጨማሪም በሌሎች ሰዎች አመለካከት ላይ ያተኩራል፡፡ሌለኛው ጥልቅ ጽብረቃተኮር መጻፍ የሚለው በስነምግባራዊ ሞራል ከፖለቲካዊ አቅጣጫ ማየት ነው (Linda Valli 1997)፡፡

በርካታ ጥናቶች በዘመኑ ቀዳሚ የጽብረቃተኮር መጻፍ አቀራረብ ሞደል ብለው ከሚጠቀሷቸው kolb (1984), Gibbi (1988) ዋና ዋናዎቹ ሲሆን ሌሎችም በእነዚህ ባለሙያዎች ስራዎች መነሻነት የራሳቸውን በማሻሻል ይጠቀሳሉ፡፡Stern(1991) እንዳብራሩት የእውቀት ግንባታ ንድፈ ሀሳብ ተከታዮች Piaget (1896-1980) ከተነሱበት ዘመን ከአራት አስርት አመታት ቦኋላ Kolb (1984) Beliwun and Dawwe Piaget የመመሪያ ሞደልን መነሻ በማድረግ ዙርመጥ የጽብረቃተኮር መጻፍ ተግባር በልምምድ መማር ሞደል አፍልቋል፡፡ ዋና ዋናዎቹ የkolb (1984) የጽብረቃተኮር መጻፍ ደረጃዎች ልምምድ በጽብረቃተኮር መጻፍ ተተርጉሞ እንዴት ግንዛቤ ይሆናል ? የሚለውን ዙርመጥ ቀላል የመማር ገለፃዎች የሚያሳዩት በፈጣን ሙከራና በአዲስ ልምድ

ምርጫ መመሪያዎች ተለውጦታይቷል፡፡ ይህ ፅንሰ ሀሳብ ግላዊ መረጃ የሚገልፅ ነው፡፡የትምህርት ማዕከል U.N.S.W (2008)ን ጠቅሰው Hampe.N (2013) እንደሚያብራሩት ከ1980ዎቹ ጀምሮ በጤናሳይንስ፤በትምህርትናአስተዳዳር በከፍተኛ ትምህርትና በሙያ ቦታዎች የጽብረቃተኮር መጻፍ የመፃፍችሎታንማሳደግመደበኛበሆነመልኩበስፋትእየተተገበረ ይገኛል፡፡

Kolb (1984) ልምድ መሰረት አድርገው ካዘጋጁት ባለአራት ደረጃ ዙርመጥ የጽብረቃተኮር መጻፍ ሞደል መጠነኛ ማሻሻል አድርገው Gibbi (1988) "በመስራትመማር" እንደሚቻል የሚያስገነዝብ ዙርመጥ የጽብረቃተኮር መጻፍ ሞደል አዘጋጅቷል፡፡ ይህ የጽብረቃተኮር መጻፍ ሞደል፤ገለጻ፤ትርጉም፤ግምገማ፤ትንተና፤መደምደሚያና ተግባራዊ እውድ የሚባሉ ስድስት ደረጃዎችን ያካተተ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ተደጋጋሚ ሞዴል በመባል ሲታወቅ የፅብረቃ ተኮር መጻፍ ሞዴሉ በቀላሉ የመማር መነሻው ድግግሞሽ ነው፡፡
እንደGiwud (2004) Finlay.L (2008) ገለፃ በአሁኑ ወቅት ትኩረት እያገኘ የመጣው የጽብረቃተኮር መጻፍ አቀራረብ የመፃፍ ችሎታን ለማስተማርና ለማለማመድ ከሚጠቀሱት ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ባለፉት አስርት አመታት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመፃፍ ችሎታን ለማዳበር በትምህርትና በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ተተገብሯል፡፡ጽብረቃተኮር መጻፍ የእለት ከእለት ትግበራ በመሆኑና በሚተገበርበት ሁነት በከፍተኛ ደረጃ ራስን በራስ የሚገመገምበት ግለሰባዊ ተግባር የሚከወንበት ለቀጣይ ተግባር አዲስ እውቀት የሚያስገኝ የህይወት ዘመን ኡደት ሂደት ነው፡፡

በተጨማሪም Ramsden.P (1992),Waten.P, Collings.J,Moon.J (2001) እንደሚያብራሩት በት/ቤቶች የጽብረቃተኮር መጻፍ ትግበራን በትብብር ተግባራዊ ማድረግ የግንዛቤን የእሳቤንና የትምህርት መረጃ ለመሰብሰብና ውጤቱን ለማስፋፋት ትልቅ አቅም ይፈጥራል፡፡ የጽብረቃተኮር መጻፍ ትግበራ ባለፉት አስርት አመታት በት/ቤቶች ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡Chaliwun (1994) ተግባራዊ የሚያደርጉት በተወሰነ የክፍል ደረጃ ወይም በተወሰነ ይዘት ላይ በተናጥል ጥረት ማድረግን ባለፉት አስርት አመታት በትብብራዊ ጽብረቃተኮር መጻፍ ተከተው ተግባራዊ ማድረጋቸው ነው፡፡

New work kidus Johannes በተማሪዎች አገልግሎት የትምህርት እገዛ ቡድን (2012) እንደገለጸው የጽብረቃተኮር መፃፍ ንድፈ ሀሳብንና ልምድን በስተሳሰረ መልኩ ይዘትን በአውድ ለመለማመድ የሚያስችል የመፃፍ ችሎታ የመማር ሂደት ሲሆን ሂደቱ ደግሞ ረቂቅ የንድፈ ሀሳብ እሳቤን ከህይወት ልምድ በሚገኝ እውቀት ትርጉም እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የጽብረቃተኮር መጻፍ የእውኑን አለም ሁነትና የአውዱን ተግባራዊነት በተገቢው ንድፈ ሀሳብ ለመተግበር ያግዛል፡፡የዚህ ጥናት ትኩረትም በጽብረቃተኮር መጻፍ የመፃፍ ትምህርትን መማር የመፃፍ ችሎታን ከማሳደግ ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር ይሆናል፡፡

## 1.2 የጥናቱመነሻችግር

William(2009) በቴክሰስ የክርስቲያን ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ላይ የጽብረቃ ተኮር መጻፍ ሞደል ተጠቅመው የተማሪዎችን ውጤታማነት ለመመርመርና የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አይነታዊ ዘዴን በመጠቀም ባጠኑት ጥናት እውቀት ግንዛቤ ባህርይ ለመመርመር ያስችላቸው ዘንድ ክፍት ጥያቄዎችን ለተማሪዎች በመስጠት ከመረሃ ግብሩ ቦኋላ ግምገማ በማካሔድ መረጃን መሰብሰብ ችለዋል፡፡ በጥናት ሂደቱ የተማሪዎች በጎፍ ቃደኝነት ያለመኖር ተጠቃሽ ችግር ቢሆንም የተለያዩ ስነ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ፊቃደኛ ሆነው ጽብረቃ ተኮር መጻፍን በተፈለገው መንገድ ለመተግበር ችለዋል፡፡ የጽብረቃ ተኮር መጻፍ አቀራረቡ ዘርፈ ብዙ መመዘኛ ነበር፡፡ ለምሳሌ ተለዋዋጭነትን አሳድጓል፡፡ ባህላዊ የሆኑ በርካታ ጉዳዮችን በማንሳት ተማሪዎች መረጃ እንዲሰጡ ማድረግ አስችሏል፡፡ ተማሪዎች በቡድን ሀሳብ መስጠትና መቀበልን ሚዘናዊነትና የተማሪዎችን ስራዎች የመተቸት አቅማቸውን አጎልብቷል፡፡ ተመራማሪው የጥናቱ ተሳታፊዎች በጽብረቃ ተኮር የፃፉትን ጽሁፍ የማንበብ አጋጣሚ ቢኖራቸውም ጽሁፎቹ ግን ተማሪዎች መማራቸውን የሚገልፁሆ ነው አልተገኙም፡፡ በዚህ መሠረት በቀጣይ ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት ቢጠና የተማሪዎችን የተለያዩየ መማር ስልት ሊያዳብር የሚችል አንድ ያልታወቀ ትርጉም ያለው አቀራረብን ማግኘት እንደሚቻል ጠቁመዋል (William 2009) ፡፡

Reacher onig (kiya) በችግር መፍትሔ ሁነት በጽብረቃ ተኮር ጆርናል ማስተማር ጠቀሜታውን 10 ተማሪዎችን ተተኳሪ በማድረግ ያደረገ ጥናት በሲንጋፖር አጥንቷል፡፡

ተመራማሪው ፍትነታዊ ዘዴ የተጠቀሙ ሲሆን አሥራ ስድስት ሳምንታት በየቀኑ ተማሪዎቻቸውን ጆርናል እንዲጽፉ አድርጓል፡፡ በዚህ ጥናት ትምህርትና ፅብረቃተኮር መጻፍ ጥብቅ ግንኙነት ማረጋገጥ ችለዋል፡፡ በችግር መፍትሔ ማሕቀፍ በመስራት መማር በተለያየ አውድ ለሚገኝ የተለያየ እውቀት ትርጉም ለመስጠት እንደሚያስችል አረጋግጠዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ ጥናቶች የሚለያዩት በአጠናን ስልት ሲሆን የሚመሳሰሉት ደግሞ ሁለቱም የተማሪዎችን የጽብረቃ ተኮር መጻፍን መሠረት አድርገው ማጥናታቸው ነው፡፡ William (2009) ጥናት በተሰጠው ጊዜ ውስን በመሆኑ የተፈለጉን ያህል ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም፡፡ በአንፃሩ Reacher Onig (kiya) በችግር መፍትሄ በፅብረቃተኮር ጆርናል የመማር ጥቅም በመመርመር የትምህርትንና የፅብረቃተኮር መጻፍን ግንኙነትን ማረጋገጥ ችለዋል፡፡

እነዚህ ሁለት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉት ደግሞ በጽብረቃ ተኮር መጻፍን መሠረት አድረገው መነሳታቸው ሲሆን በተለይ ከReacheronig (Kiya) በአጠናን ስልት ይመሳሰላል፡፡ እንዲሁም Linda.E.Martin,sherlilziaker (2009) በዝቅተኛ ክፍል ተማሪዎችን በዕድሜ በመለያየትባካሔዱትየምርምር ውጤት ተጠኚ ተማሪዎቻቸው ውጤታማ መሆናቸውንአረጋግጠዋል፡፡ በዚህም ጽብረቃ ተኮርን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎችን ከማስተማር በፊት በመጀመሪያ ፍላጎታቸውን ማሰስ

እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል፡፡ ከዚያ በመቀጠልም ስልጠና መስጠት ተለዋዋጭ ሁነት መፍጠር ማንበብና መፃፍን ማስተሳሰር በጽብረ ቃተኮር መጻፍ ለማስተማር አብይ ተግባራት መሆናቸውን ለመጠቆም ይሆናል፡፡ እነዚህም ሂደታዊ ተግባራት የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ በማዳበር ረገድ ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጡ አሳይተዋል፡፡

በጽብረቃ ተኮር መጻፍ ትግበራ ወቅት ግንዛቤያዊና ንድፈሀሳባዊ ውስብስብችግሮችን አከራካሪ የሆኑ ነባራዊና ግለሰባዊ መረጃዎችን በትኩረት መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በጽብረቃ ተኮር መጻፍ ተግባራዊነትን ከሚቃወሙ አካላት ጋር ስነምግባራዊ ሙያዊ ስነትምህርታዊ ግንዛቤያዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ትኩረት ሰጥቶ ለመወያየት ይሆናል፡፡ አስፈፃሚው አካል በጥልቀትና በትዕዛዛዊ መልኩ የትምህርት ግብዓቶችን ከመጠቀሙ በፊት ትክክለኛነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል (Linda, Finlay 2008) ፡፡
ውጤታማ ትምህርት ለመስጠት በጽብረቃ ተኮር መጻፍ ተግባር ተግባራትን ማሳደግ፤ መስራትም ሆነ ማስተማር ከበድ ነው፡፡ ጽብረቃ ተኮር መጻፍ ተፈፃሚነቱን አምታችና ውስብስብ ከሚያደርጉት ባህርያቱ መካከል አንዱ ጽብረቃው በሂደቱ መጨረሻ የሌለው በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ትግበራው ባልተለመደው መልኩ በብዙ አቅጣጫ ችግር ቢያጋጥመው ሃላፍነትን ወስዶ ማስቀጠል ይገባል (Linda,Finlay, 2009) ፡፡

እንደ Linda,Finlay(2008) አገላለጽ  የጽብረቃ ተኮር መጻፍ ተተግባሪ አላባውያን ለምሳሌ፤ ሙያዊ ጥበብ ተተኳሪ ትምህርት ችሎታ ተያያዥ ትምህርታዊ ዘርፎች ዝቅተኛ ግንዛቤ ቢሰጣቸው ትችት ቢበዛባቸው ፈፃሚዎች አካብደው ቢመለከቷቸው ከትግበራ ሊያግዱ አይገባም፡፡ ምክንያቱም የጽብረቃ ተኮር ትግበራ የበርካታ አውድ ዝርዝር ይሆናል፡፡ ምናልባትም የሚያንጸባርቅበት ርዕሰ ጉዳይና ፍላጎት ሊለያይ ቢችልም ጽብረቃን ለመተግበር የተለያየ ዘዴ የተለያየ ጊዜ የተለያየ ሁነት ወይም አካባቢ አደረጃጀት ግንኙነት ያስፈልጋል፡፡
Finlay (2008) እንደሚያስረዱት በጽብረቃ ተኮር መጻፍ ሂደት ተሳታፊዎች ከራሳቸው ይልቅ በሰፊው ማህበራዊ አውድ ላይም እንዲያተኩሩ ማድረግ ትረት የሚሻና አከራካሪ ጉዳይ ሆኗል፡፡
ጽብረቃ ተኮር መጻፍ እንደት? መቼ? የት? ለምን? ተግባራዊ መሆን አለበት? የሚሉት ምምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ጽብረቃ ተኮርን ባለሙያዎቹ ከጊዜ እጥረት አኳያ ያለምንም ተገቢ ሙከራ ያለጥልቅ እሳቤ ቴክኒካልና ቀላል በሆነ መንገድ ተግባራዊ ያደርጉት ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ በተለይም መፃፍን በፅብረቃ ተኮር መጻፍ ለማለማመድ ጠቀሜታውንና እጥረቱን መመርመር በቂ መረጃ ለማግኘት ያስቸግራል፡፡ በመሆኑም የፅብረቃ ተኮር መጻፍን መመርመር ገና ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በጽብረቃ ተኮር መፃፍን ለማስተማርና ለማዳበር የሚቀርበውን የጽብረቃ ተኮር  ትግበራ ጊዜን አስፈላጊ አላባዉያንን (ግብአት) አጋጣሚዎችንና ስነዘዴዎችን ለጽብረቃ ተኮር መጻፍ በሚመጥን ጥራት ማመቻቸት የጥልቅትን ተና ችሎታ ማዳበር ቀጥሎም ለጽብረቃው ተገቢ የሆነ አውድ ለመፍጠ ርያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ላይ ምቁልፍ ጥያቄዎችም ጽብረቃ እንዴት ውጤታማ ይሆናል? የሙያው ባለቤቶች እንዴት ይረዱታል? የሚሉት ሲሆኑ የጽብረቃ ተኮር ትግበራ ሙሉ ሊሆን የሚቻለው አቅምን በሙሉ ተጠቅሞ ምቹ ሁኔታ ባይኖርም ለህሊና ተገዝቶ ተግባራቱን መፈጸም ሲቻል ነው (Finlay 2008, 2009) ፡፡

Linda.E.Martin, Sherliziaker, (2009) በጽብረቃ ተኮር መጻፍ ጥናት ያተኮረው ተማሪዎችን በዕድሜ በመከፋፈልና ፍላጎታቸውን በማሰስ ላይ ሲሆን የጽብረቃ ትግበራው እንዴት ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ለማሳየት ይሆናል፡፡ ጥናቱ ከዚህ ጥናት የሚለየውም ተማሪዎችን በእድሜ በማከፋፈል ከ (Finlay 2008, 2009) የሚለየው በትኩረት ነጥቡ ነዉ፡፡

N.A.E.P.Apelib and Langer (2007) ከ1969-1970 በሰበሰቡት መረጃ እንዳረጋገጡት በአሜሪካ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎችንና መምህራን ለመፃፍ ችሎታ ያላቸው ግምት ከፍተኛ ሲሆን የመፃፍ ችሎታቸውንም ከጊዜ ወደ ጊዜ ያዳብራሉ፡፡ በ2002 የተመሠረተ የኮሌጅ ቆይታቸው የመፃፍ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ በፖሊስ ተግባራትን ለማከናወን ነው፡፡ በመሆኑም በ1980ዎቹ በተሰበሰበ አዋህደው መማራቸው ከፍተኛ መሻሻል የመጣ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም የእድገቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በ2009 ባደረጉት ቅኝታዊ ጥናት ውጤቱ በተቀራኒዉ ቀንሶ የተገኘ ሲሆን ምክንያቱም ደግሞ ተማሪዎች መፃፍን የሚማሩት በኮምፒዩተር በታገዘ ጽብረቃ ተኮር በመሆኑ ግለሰባዊ ልምምድና ጥረት ያልታከለበት ስራበ ዘመናዊ መሣሪያ ታግዘው በመፃፋቸው መሆኑን Apelib.and Langer (2009) ለማረጋገጥ ችለዋል፡፡

N.A.E.P. አገር አቀፍ የትምህርት ማበልጸጊያ ማህበር (1992) በተለያዩ ጊዜያት ተማሪዎችን መፃፍን መመሪያ ተኮር ከማድረግ ይልቅ መፃፍን በተከታታይ ምዘና ማድረግ ያለውን ሁኔታዊ ለዉጥ የአሰሳ ጥናት አጥንተዋል፡፡ በጥናታቸውም ጥናቱ የተጠናው ዘመናዊ ዘዴ ቢሆን ኖሮ የተማሪዎችን የመፃፍ ለውጥና አመለካከት በመቶኛ ደረጃ አውጥቶ ማሳየት ይቻል ነበር በማለት የጥናታቸን ድክመት አመልክተዋል፡፡ በተጨማሪም ቅኝታዊ በመሆኑ አንድ ዋና ውጤት እንጂ የችግሩን ምክንያትና ዝርዝር መረጃ ማብራራት አልተቻለም በማለት ለቀጣይ ምርምር መነሻ እንዲሆን ለማሳየት ጠቁመዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ የቅኝት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር በአጠናን ስልትና ስነዘዴ መመሳሰል ባይኖራቸዉም የመፃፍ ችሎታን መሠረት አድረገው የተጠኑ በመሆናቸውና የዚህ ጥናት አላማ የመፃፍ ችሎታን ለማደበር በመሆኑ ጥናቶች መነሻ መረጃ ሊሰጡይችላሉ በሚል ተካተዋል፡፡ በመሆኑ ምከጥናቶቹ መረዳት እንደተቻለው የመፃፍ ችሎታን ለማዳበር የሚጠኑ ጥናቶች ፍትነታዊ መሆን እንዳለበት ነዉ N.A.E.P. አገር አቀፍ የትምህርት ማበልጸጊያ ማህበር (1992)፡፡ በጽብረቃ ተኮር መጻፍ ትግበራ መፃፍን መማር የሚያመጣውን ውጤት በተመለከተ በውጭ ሀገር ከተሰሩ ጥናቶችየ William (2009) እና የReacheronig (kiya) አዎንታዊ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል አመላክተዋል፡፡ በአንፃሩ Linda,Finlay (2008,2009) በመስኩ የሚደረጉ ጥናቶችን ውጤታማ ለማድረግ እጅግ እልህ አስጨራሽ ተግባራት እንደሚኖሩት ገልፀዋል፡፡

Epsten and Hundet (2000) Levin and cernright (2008)ን በመጥቀስ Hampe.N (2013) እንዳብራሩት ጽብረቃ ተኮር መጻፍ የተከታታይ የሙያ ዕድገት መሻሻል ለማምጣት የሚያስችል ጅማሮ ነው፡፡ ምንም እንኳ አንዳንድ ባለሙያዎች ውስጣዊ ችሎታ ትግበራ ነው ብለው ባያምኑም ግለሰባዊ እሳቤን ልምድን በከፍተኛ ደረጃ መግለጽና ማሳወቅ እንደሚቻል ያብራራሉ፡፡

በተጨማሪም ጽብረቃተኮር መጻፍን ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት የሚሏቸዉን ጉደዮች Brod (2008)ን ዋቢ በማድረግ Hampe.N (2013) የተለያየ ዳራ መኖር ባህል ትምህርት ቤተሰብ ስራ በራስ መተማመን ቁርጠኝነት ስልት የኑሮ ደረጃ የአለማችን ሁኔታ የፍላጎት ልዩነት ተነሳሶት ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ናቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡

በሀገር ውስጥ ግን በጽብረቃ ተኮር መጻፍ ትግበራ መፃፍን ማስተማር በተመለከተ የተሰሩ ጥናቶችን ከታዩት የመረጃ ምንጮችማግኘት አልተቻለም፡፡

ከላይ የተለያዩ ተመራማሪዎች የቀረቡት አስተያየቶችና የጥናትውጤቶች ሲጠቃለሉ ግን የመፃፍ ችሎታን ለማዳበር እጅግ ከፍተኛየሆነ ጥረት ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም ጽብረቃ ተኮር መጻፍ በባህሪው ውስብስብ በመሆኑ ችሎታውን ለማሳደግ የሚነሱ ጉዳዮችም ውስብስብ መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

በተጨማሪም የጽብረቃ ተኮር መጻፍ ትግበራ ታጋሽነትንና ጥረትን ጊዜንና ጉልበትን የሚጠይቅ አፈፃጸም ያለው መሆኑ ያመለክታሉ፡፡ ሆኖም ትግበራው የሚፈልገውን ቅደመ ሁኔታ ማሟላት ከተቻለ በጽብረቃ ተኮር መጻፍ ትምህርትን መማር የመፃፍ ችሎታን ማሻሻል የሚያስችሉ ፍንጮች ያሉ ይመስላል፡፡ የፅብረቃን የክፍል ትግበራ በተመለከተ ያጋጥማሉ የሚባሉ ተፅዕኖ ፈጣሪ ተላውጦዎችን በምን መልኩ ማበረታታት እንደሚቻል በጥናቶች የተደገፈ መፍትሄ ከማመላከት አኳያ ክፍተት አለ፡፡ በርካታ ጥናቶች ፅብረቃ ተኮር መጻፍን ተጠቅመው ባህልን ሳይንስን መርምረዋል፡፡ በምርምር ሂደቱ መረጃዎችን በመሰብሰብ የሚጠቀሙበት ክፍት ጥያቄዎች በመሆኑ ተሳታፊዎች መረጃዎችን የሚሰጡ በፅብረቃ ተኮር መጻፍ ነው፡፡ የተሳታፊዎች ፅሁፍ የሚመረምረው ለጥያቄዎች ከሚሰጡ ምላሽ ይዘት አንፃር እንጂ የእነሱን የመፃፍ ችሎታ ከመመዘን አንፃር አይደለም፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ርዕስ ምርምር ለማካሄድ ሲታሰብ በአጥኝው በተካሄደው የቀደምት ቅኝት በፅብረቃተኮር መጻፍ ማስተማር ላይ በቀጥታ የተሰራ ጥናት ባይገኝም ከላይ የተጠቀሱት የውጭ ሀገር ጥናቶች በፅብረቃተኮር መጻፍ ቋንቋን ለማስተማር ያለው ፋይዳ ሲያጠኑ በፅብረቃተኮር መፃፍን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል አጥንተዋል፡፡

ይህ ጉዳይ ተጠንቶ ያልተቋጨ መሆኑና ተጨማሪ ጥናት ሊደረግበት እንደሚገባ አጥኚዎቹ የገለጹ ሲሆን በፅብረቃተኮር መጻፍ ማስተማር በሚል ርዕስ በሀገራችን ከተካሄዱ የምርምር ስራዎችም አጥኚው ባከናወነው የቀደምት ጥናቶች ያልተገኘ በመሆኑ ለአጥኚው በዚህ ርዕስ ምርምር ለማካሄድ አነሳስ ምክንያት ሆኖዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አጥኚው ባስተማረው ዓመታት  አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በፅብረቃተኮር መጻፍ የመፃፍ ስራ ሲሰጣቸው ሀሳብ በማጣት ሲቸገሩና ለመፃፍ ችሎታ ሲያጡ ቢፅፉም በአብዘኛው ምን ለማለት እንዲፈልጉ  እንኳን ለመረዳት አስቸጋሪና ውጤት እንዲያገኝ ብቻ የሚተገብሩት መሆኑን አስተውለዋል፡፡

ለዚህም አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በፅብረቃተኮር መጻፍ በማስተማር የመፃፍ ችሎታንበማጎልበትይቻል ይሆን?የሚለውን ለመመርመር አጥኚው ወደዚህ ርዕስ ተገፋፍተዋል፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ ጥያቄው የሚከተለው ነው፡፡

1. በፅብረቃ ተኮር መጻፍ የመፃፍ ችሎታን በማሳደግ ረገድ ያለዉን አስተዋፅኦ አለውን?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ፅብረቃዊ ተኮር መጻፍ የመፃፍ ችሎታ የማሳደግ ረገድ ያለውን አስተዋፅኦ መፈተሽ ሲሆን ዝርዝር ዓላማውም የሚከተለው ነዉ፡፡

1. ፅብረቃ ተኮር መጻፍ የመፃፍ ችሎታን በማሳደግ ረገድ አስተዋጽኦ ለመመርመር፡፡

## 1.4 የጥናቱአስፈላጊነት

ይህ ጥናት በፅብረቃ ተኮር መጻፍ የመፃፍ ችሎታለማዳበር ያለውንአስተዋፅኦስለሚመለከት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች በማስገኘት ረገድ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

በጽብረቃተኮር መጻፍ የመፃፍ ችሎታን ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራዊ አሰራሮችን  ለመምህራን ባለሙያዎች ለተማሪዎች ለማስተዋወቅ ነው፡፡ተማሪዎች በመማር ሂደት ንድፈ ሀሳብን ወደ ተግባር ለመቀየር የሚችሉበትን መንገድ ሊያመላክት ስለሚችልከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያለውን ጥናት ለሚጠኑ ተመራማሪዎች መረጃ በመስጠት ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱወሰን

ጥናቱ ከቦታና ከትምህርት ቤት አንጻር ያተኮረው በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን በወረ ጅሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ከክፍል ደረጃና ከተማሪዎች አንጻርም የክፍል ደረጃው በአላማ ተኮር ናሙና እንዲሁም በተራ/በቀላል የእጣ ናሙና ስልት በተመረጡ ሁለት የመመሪያ ክፍሎች በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ጥናቱም ተማሪዎች ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ልምምድ ካደረጉ በኋላ ያሉበትን ደረጃ በማነጻጸር የተማሪዎችን ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያላቸውን አስተዋጽኦ በንጽጽር ፈትሿል፡፡ እንዲሁም የተማሪዎችን ጽብረቃ ተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያላቸው አስተዋጽኦ ተፈትሿል፡፡

በዚህ ጥናት Rolf ሌሎች (2011) ያሻሻሉት የጥልቅ ጽብረቃተኮር መጻፍ ሞደል የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማዳበር በተመረጠው የጽብረቃተኮር መጻፍ ተሳታፍዎችን ለማስተማር አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡

ይህ ሞደል የተመረጠበት ምክንያት ጥልቅ ጽብረቃተኮር መጻፍ በስነምግባራዊ መስፈርት ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ለመስጠት ስለሚያስችል ረቂቅ የንድፈ ሀሳብ እሳቤ ከህይወት በሚገኝ እውቀት ትርጉም እንዲኖረው ትልም

አቅም እንዲፈጥር ነው፡፡ስለሆነም ሞደሉን ቢለማመዱ በዙርመጥ ልምምድ የእውኑን አለም ሁነት የአውዱን ተግባራዊነት በተገቢው ንድፈ ሀሳብ ለመተግበር ያስችለዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ የRolf በጥልቅ ጽብረቃተኮር መጻፍ ሞደል ትኩረቱ ትምህርቱን ከማህበራዊ ከስነምግባር ከሞራልና ከፖለቲካ አቅጣጫ በማየት ንድፈ ሀሳብንና ተደጋጋሚ ልምምድን በስተሳሰረ መልኩ ይዘትን በአውድ ለማለማመድ የሚያስችል በመሆኑ ጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ያስችላል ከሚል እሳቤ ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

በዚህ ጥናት ሁለቱም ቡድኖች በተለያዩ ትምህርትቤቶች እንዲማሩ ቢደረግ በትምህርትቤቱ አካባቢና በመምህራን ልዩነት የተነሳ በጥናቱ ውጤት ላይ ተፅዕኖ እንዳይደርስ በመስጋት ሁለቱም ቡድኖች በአንድ ትምህርት ቤት የሚገኙ ናቸው፡፡በመሆኑም በዚህ ጥናት የተለያዩ ፅብረቃተኮር መፃፍ እየተሰጣቸው የመፃፍ ችሎታን ልምምድ ያደረጉ ቡድኖች የተለማመዱባቸው ወረቀቶች ከእያንዳንዱ ክፍለጊዜ በኋላ በመምህሩ የተያዙ በመሆናቸው አንዱ ሌላው የተሰጠውን ፅብረቃተኮር መፃፍ አግኝቶ የመለማመድ እድሉን በመቀነስ የተጋቦት ተፅዕኖውን ለመቆጣጠር ስለማይቻል በጥናቱ ውጤት ላይ ተፅዕኖ አሳድሮ ሊሆን ይችላል፡፡በአጠቃላይ በጥናት ሂደቱ በፅብረቃተኮር መፃፍ መፃፍን በማስተማር ረገድ አጥኚው ካገኘው ጥናቶች መካከል በአገር ውስጥ የተሰሩ ጥናቶች ባለማግኘቱ ከአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ የተጠና ጥናት ባልካተቱ አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ውስንነት ሊታይበት ይችላል፡፡

## 1.7 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳብ አጠቃቀም ብያኔ

1. **ፅብረቃ ተኮር፤** በዚህ ጥናት በፅብረቃ ተኮር የተከሰቱ ሁነቶኛ እንዴት? ለምን? እንደተከሰቱ የሚገልፅበት፣ ሁነቶች በመከሰታቸው የተገኘ እውቀት ከቀደመ ልምድ ጋር በማገናዘብ ርዕስ ጉዳያችን በተለያየ እይታና ግንዛቤ በፅሁፍ የሚገለፅበት በድርጊቶች ተከታታይነት ላይ በማተኮር በጥልቀት የሚተነተንበት፣ ከተከሰተ ክስተት ምን መማርተቻለ ? ለወደፊቱስ ምን ማድረግ ይገባል? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥበት መፃፍን የመማሪያ ብልሃት ነው፡፡

2. **የመፃፍ ችሎታ፤** በዚህ ጥናት የመልዕክቱን የሀሳብ ፍሰት በጠበቀ መልኩ የሀሳቡን አንድነትና ግጥምጥሞነት ጠብቆ ርዕሰ ጉዳይ እንዴት? ለምንሆነ? ርዕሰ ጉዳዩ በሚከሰቱ ምን ትምህርት ተገኘ ምን ክፍተት ተከሰተ? ችግሩንስ ወደ ፊት እንዴት ማስተካከል ይቻላል? በማለት አብራርቶ ሀሳብን በፅሁፍ ማስፈር መቻል ነው፡፡

## ምዕራፍሁለት፤የተዛማጅ ድርሳና ትክለሳ .

በምዕራፍ አንድ እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጽብረቃተኮር መጻፍ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ በማሳደግ ረገድ አስተዋጽኦ መኖሩን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ዓላማ ለማሳካትም ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በጥልቀት ይዳሰሳሉ፡፡በዚህ መሰረት በመጀመሪያ የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ማሕቀፍ ይቀርባል፡፡

### 2.1 በጽብረቃ ተኮር ናየመጻፍ ችሎታ ትስስር

ጽብረቃ ተኮርና የመፃፍም ዘና ውጤታማ የመፃፍ አዕምሮአዊ እውቀት በትምህርታዊ እይታ ምን አይነት እሳቤ አውቃለሁ? የሚለውን እይታ ይጠይቃል፡፡ በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የመፃፍ ችሎታ የውስብስብ እውቀት ተግባራትን የያዘነው፡፡

Burton.J እና ሌሎች(2009)፡፡ Wato.P; C0llings.J; Moon.J(2001) እንደ ገለፁት የጽብረቃ ተኮር የበርከታ ተግባራት ምንጭ ነው፡፡ በመሆኑም በፅብረቃ ተኮር በመማሪያ ክፍል ተግባራዊ ማድረግ እጅግ ውስብስብ የሆነ ችግርና ውጡታማነትን ሌሎች በማሳየት ገፅታ ውስጥ ነው፡፡ የፅብረቃተኮር እጅግ አስደናቂና ማህበራዊ፡ ተግባር ነው፡፡ስለዚህ መፃፍ ያለፅብራቃ አጋዥነት ስኬታማ ሊሆን አይችልም Burton.J እና (2009)፡፡

Koners (1982), Kiroul (1998) ን ጠቅሰው Paul.Deane (2008) እንደሚያብራሩት ጥንታዊ የመፃፍ ትምህርት የሚያተኩረው በቅርጽ ላይ በተለይም በገላጭና አመዛዛኝ የአፃፃፍ ስልት ትምህርታዊ አወቃቀር ላይ ሲሆን ተማሪው በክፍል ውስጥ የተፈጠሩ ሰው ሰራሽ አውዶችን ተጠቅሞ ቅርፅን ሊገነቡ የሚችሉ አለባዎችን በመገጣጠም መፃፍ ችሏልን? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ላይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምንም እንኳን ጎጅ ባይሆን ምተማሪው በመፃፍ ችሎታ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስፈልገውን ንዑስ ክሂል አያሳይም፡፡ መፃፍ ከዲስኮርስ ጋር በተያያዘ አንደበታዊ አፍልቆት ችሎታን የሚጠይቅ እጅግ ሰፊና ውስብስብ ነው፡፡ ሰዎች የሚፅፉ በሚኖሩበት በማህበረሰብ በሚኖራቸው የተግባቦት ዓላማ ነው፡፡ በትምህርት ቤቶችም መፃፍ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ከክፍል ትምህርቱ ባሻገር ተማሪዎች ሊያፈልቁት የሚገባ አሀድ በተለያዩ ዓላማ ሰፊ ክበብ ያለውና አብዛኛውን ማህበራዊ አውድ ማካተት ሲችል ነው፡፡

Laura hulick (Kiya) የመፃፍ ችሎታ ለማዳበርና በመፃፍ ችሎታ ላይ ያላቸውን  አመለካከት ለመመርመር በፖርክፎረስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በ6 ወንድና በ12 ሴት በድምሩ በ18 ተማሪዎች ላይ በተደረገ ጥናት ላይ ተማሪዎች ተጨማሪ የንባብ ቁሳቁሶችን ያደሉ ሲሆን ለሁለት ተማሪዎች  በምክር አግዘዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች የመፃፍ ችሎታቸው ዝቅተኛና በልምድ፡ ጊዜ፡ ከአማካይ፡ ችሎታ፡ በታች፡ የነበሩት፡ የመፃፍ፡ ፍላጎታቸው፡ ዝቅ ብሎ ታይቷል፡፡ እያንዳንዱ ተሳታፊ የተለያዩ ምርጫ የነበረው ሲሆን የተለያየም ጋቤ ምላሽና ዕገዛ ያስፈለገው ነበር፡፡ ለተማሪዎች በልምምድ ወቅት የተሰጣቸው ስልጠና በፅሁፋቸው ጥራት ላይያሳደረው ተፅዕኖ ግልፅ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ከገላጭ ጽሁፍ ይልቅ ተራክ ጽሁፍ ላይ የተሻለ ዉጤት አሳይቷል፡፡

በተደረገው ምልከታ ማረጋገጥ እንደተቻለው ለተማሪዎች የሚሰጡ  አሀዶች እጅግ ውስን መሆን ተማሪዎች በፍጥነት ወደ ልምምድ እንዲገቡ ያደረጋቸዋል፡፡ ለሚለው ተጨባጭ ማስረጃ ማግኘት አልቻልኩም ይላሉ፡፡ ለተማሪዎች የፅሁፍ ዘውግ  እንዲመርጡ ማድረግ ከሚፅፉት ጋር ምንም አይነት ዝምድና የለውም፡፡ ሆኖም የዘውግ አይነቶች በተማሪዎች ውጤታነት ላይ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ ለመነሻ ሊሆን የሚችል አውድ መስጠት የተማሪዎችን ለመፃፍ ያላቸውን ፍላጎት ይጨምራል፡፡ በዳሰሳ መጠይቁ የሰጡትም ላሽአሉታዊ የሆነውም እንኳ በሂደት ለመፃፍ መረጃ ሊሰጥ የሚችል አውድ መኖሩ ጥሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

Laura hulick (kiya) በአጠቃላይ በተሳታፊዎች ላይ ባደረጉት ክትትልና ምልከታ ተማረዎች ከልምምድ በኋላ ምንም አይነት ጭንቀት እንደማይታይባቸው አረጋግጠዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ያለውን  ለመተረክ ለመግለፅና ለመተንተን የነበራቸውን ፍላጎት ከፍተኛ ነበር፡፡ ሆኖም በቀጣይ ጥናቶች ሲታዩና ሊመለሱ የሚገባቸው ጥያቄዎች ብለው ከዘረዘሯቸው መካከል የተማሪዎች ማህበራዊ ክሂሎት በመፃፍ ችሎታቸውን ፍላጎታቸው ላይ ያለው አስተዋፅኦ የተማሪዎች መፃፍ አወቃቀር በፅሁፋቸው ጥራትና ስፋት  ላይ

ያለው ተፅዕኖ የዕለት ከዕለት ልምምዳቸው በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ እድገትና ጥራት ላይ ያለው ተፅዕኖ ምንድን ነው የሚሉ ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡

በተጨማሪም ፅብረቃ ተኮር በመማሪያ ክፍል የሚፃፍ የተለያየ የፅሁፍ ስራን የሚካተት ሲሆን ስምስተር ከሚጠይቅ ሰፊ ፅሁፍ እስከ የእለት የክፍል የፅሀፍ ስራ ያጠቃልላል በማለት የሚያብራሩት Roos.N (2011) በዩናይትድ እስቴትስ ወታደራዊ አካዳሚ West Penti.N.Y በፅብረቃ ተኮር መጻፍ የተማሪዎች ጥልቅ እሳቤ ችሎታና እጅግ የተሻለ የመፃፍ ችሎታ እንዴት ለማዳበር ይችላል? በሚል ርዕስ ባካሄዱት የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት እንዳረጋገጡት በፅብረቃ ተኮር መጻፍ የተማሪዎችን ማስተማር የተማሪዎቸን የፅሁፍ ችሎታ በመጠንም ሆነ በጥራት ስለሚያሻሽል ተማሪዎች የተመለከቱትንም ሆነ የሰሙትን በመግለፅ በዘለለ ጠለቅ ያለ ፅሁፍ እንዲፅፉ ያበረተታል፡፡

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን ነባራዊ ሀሳብ አደራጅተው በመተንተንና በመተርጎም ስሜት በሚሰጥ መልኩ እንዲፅፉ ለማበረታታት ያበረታታል፡፡ Jun dewey (kiya)ን ጠቅሰው Roos.N(2011) እንደሚያብራሩት ተማሪዎች ከተሰጣቸው መረጃ ጠቃሚውንና የሚያስፈልገው መረጃ ለመለየት ስለሚያሲችል ነዉና አያይዘውም በመማሪያ ክፍል ውስጥ በፅብረቃ ተኮር ለመተግበር በትግበራው ዙሪያ የተለያዩ መረጃዎችን ከአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ በማሻሻል መስጠት የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ያጠናክራል፡፡ ፅብረቃ ተኮር መጻፍ ልምምዱ በፊት ለተማሪዎች መነሻ ሊሆን የሚችል ሀሳብ አውድ መስጠት በተሰጣቸው ነባራዊ እውነታ ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲያብራሩ እንዲተነትኑ ይረዳቸዋል፡፡ የተለያዩ ተመራማሪዎች እንደሚገልፁት በፅብረቃ ተኮር መጻፍ በተለያዩ መንገድ ይመዝናሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ ሊያተኩሩበት የሚገባዉ ነጥብና ከእነርሱ የሚጠበቀው ውጤት በቅድሚያ ይገለፅላቸዋል፡፡በተጨማሪም ምጋቤ ምላሽ ሲሰጣቸው በጥልቀት ሊተነተኑና ሊገለጹ በሚያስችላቸዉ መንገድ መሆን ይገባል (Roos.N 2011)፡፡

B.N.Sen (2010) በጽብረቃተኮር መጻፍና መፃፍ ችሎታ የተማሪዎችን የጽብረቃጽሁፍ በመተንተን የተማሪዎችን ዉጤት መርምረው ይገልፃሉ፡፡በጥናታቸዉ ከ31 የቤተመፃህፍት አስተዳደር ተማሪዎች መካከል በጥናቱ ለመሳተፍ የተሰማሙ ከ21 ዓመት እድሜ በላይ የሆኑ ሰባት ወንዶችና 15 ሴቶች በአጠቃላይ 22 ተማሪዎች ተሳትፈዋል፡፡ከጥቅምት- 2008-ግንቦት 2009 እ.አ.አ.ለስምንት ወራት 116 በጽብረቃተኮር ጽሁፎችን አጽፈዋል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ለጽብረቃተኮር መጻፍ አዲስ ሲሆኑ እያንደንዱ ተማሪ ከፍተኛ 7 ዝቅተኛ 4 በአማካይ 5 የተለያዩ ጽብረቃተኮር ጽሁፎች ጽፈዋል፡፡የተጠቀሙበት መረጃ መተንተኛ Girant (2007) and moon (2007) የጽብረቃተኮር መጻፍ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግና S.p.S.S ካይ ስኩየርን በመጠቀም ነው፡፡B.N.Sen (2010) እንደገለፁት የጥናቱ ውስንነት ተሳታፍዎቹ በሚለማመዱበት ወቅት የሚጽፉት በቃላት መገደቡ የመፍጠር አቅማቸውን ይገድባል ብለዋል፡፡ምንም እንኳ መፃፍ ውስብስብ በመሆኑ ለማስተዳደር ትኩረት የሚጠይቅ ቢሆንም የተማሪዎች የጽሁፍ ስራ በቃላት ብዛት መገደቡ የተሳታፍዎችን

የመፃፍ ችሎታ ይገድባል በማለት ያብራራሉ፡፡ተማሪዎች በሂደት እያዳበሩት የመጡ ቢሆንም የጽብረቃተኮር መጻፍ አዲስ ከመሆናቸዉ የተነሳ በጽሁፍ ጥራት ላይ ተጽዕኖ የፈጠረ ሲሆን የተሳታፍዎች የጽሁፍ ስራ ጥራት የተለያዩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ እንደተረጋገጠው ተማሪዎች በጽብረቃተኮር መጻፍ ሂደት አውድን መግለጽ ልምዳቸውን መግለጽ በጥቅሉ በጽብረቃ ሂደት የተሳተፉበትን የቀደመ ልምድ ወቅታዊ ግንዛቤያቸውንና ቀጣይ አሰራራቸውን በግልጽ ተገንዝቦ የመፃፍ ችሎታቸውን አብራርቶ መፃፍን አዳብረዋል፡፡

በተጨማሪም ጽብረቃተኮር በወጉ የሚዳብርና በተከታታይ ልምምድ የመጻፍ ችሎታ የሚዳብር መሆኑን ያሳያል፡፡በመደበኛ ትምህርቱ እራስን የማሳደግ ፍላጎትን ለማሳደግ ትክክለኛ ጥልቅ እይታን ለማዳበር አዕምሮአዊ እይታን ለማግኘት የመወሰን አቅም ለማሳደግ አዎንታዊ ውጤት የታየ ሲሆን መደበኛ ባልሆነ ትምህርትና በጽብረቃተኮር መጻፍ መካከል ያለዉን ልዩነት በመተንተን ውስን የሆነ መረጃ ቢኖርም ያን ያህል የተለየና የታወቀ አይደለም፡፡

B.N.Sen (2010) እንደሚያብራሩት ለተሳታፍዎች ጽብረቃተኮር መጻፍ የሚያግዙ የተለያዩ የጽሁፍ አውዶች ገለፃዎችና ስልጠናዎች የተሰጠ ሲሆን ለጽብረቃተኮር መጻፍ ችሎታቸውና ለግንዛቤያቸው እድገት ጥሩ እገዛ አድርጎላቸዋል፡፡በጽብረቃተኮር መጻፍ ትግበራ በመጀመሪያ ግልጽ ያልሆነ ሲሆን ለተማሪዎች ግልጽ ለማድረግ በርካታ ምሳሌዎችን መስጠትና እገዛ ማድረግ አስፈልጓል፡፡

በተደረገላቸው እገዛ በጽብረቃተኮር ችሎታቸውን ማዳበር ችሎዋል፡፡በጽብረቃተኮር መፃፍ ችሎታ ተማሪዎች ባላቸው የመማር ስልት በተለያየ ዘዴና እንደፍላጎታቸው አንጸባርቋል በማለት አብራርቷል (B.N.Sen 2010) ፡፡

U.K.በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥልቅ ጽብረቃተኮር መጻፍን አስፈላጊነት ማሳደግ ቁልፍ ችሎታ አጀንዳ ሆኖዋል፡፡የሚሉት Trekking (2002) ባካሄዱት ጥናት እንዳብራሩት የስራ ባልደረቦችንና ተማሪዎች የጽብረቃተኮር መጻፍ ደረጃዎችንና የመፃፍ ችሎታን በማደበር እንደት ጽብረቃተኮርን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ግልጽ ሊሆንላቸው ይገባል፡፡ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር የሚያፈልገው የመፃፍ ምዘና ማወቅና ግንዛቤውን ማዳበር ያስፈልጋቸዋል፡፡

Trekking (2002) በጽብረቃተኮር መጻፍ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ማሳደግ በሚል ርዕስ በU.K.በፖርትስ ማውዝ ዩንቨርስቲ ባካሄዱት ጥናት እንደሚያብራሩት ላይ የስራ ባልደረቦቻቸው ለ1.00 ሰዓት ያህል ለ180 የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለ2.00 ሰዓት ያህል በጽብረቃተኮር መጻፍ ልምምዱ በፊት ስልጠና የሰጡ ሲሆን የጽብረቃተኮር መጻፍ ሞዴሎችን ለማስተዋወቅና ስለጥናቱና ልምምዱ ዓላማ ግንዛቤ ለመፍጠር አስችሏል፡፡የጥናቱ ተሳታፍዎች ለ10 ሳምንታት በጽብረቃተኮር መጻፍን የተለማመዱ ሲሆን የመፃፍ ችሎታቸው ከማዳበሩ በተጨማሪ በትምህርት አመቱ ማጠቃለያ ለሰሩት ለድህረ ምረቃ ዲሰርቴሽ ከፍተኛ እገዛ አድርጎላቿል በማለት ያብራራሉ፡፡

Rodgers carol (2002) እንዳብራሩት ጽብረቃተኮር መጻፍ በመጀመሪያ How We Think demockracy and education experiences ከሚሉ ሁለት የJunduwe መጽሀፎች ወስደን ስናብራራ ጽብረቃተኮር መጻፍ በራሱ የመጨረሻ ሳይሆን የተገኘን መረጃ ልምድ የንድፈ ሀሳብ መሰረት ወዳለውና ትርጉም ወዳለው ልምድ ለማሸጋገር የሚጠቅም ንድፈ ሀሳብን የሚያረጋግጥ ለማህበረሰብና ለግለሰብ የሞራል እድገት ለማሳደግ አላማ የሚውል መሳሪያ ነው፡፡በተመሳሳይ ጽብረቃተኮር መጻፍ መማር በራሱ የመደበኛ ትምህርት ማበልጸግያ ብቻ ሳይሆን በመስራት ለመማር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል በማለት Moon.J (2004) ይገልፃሉ፡፡

Boman (2014) በታላቁ ካናዳውያን ዩንቨርሲቲ በእጣ ከተመረጡት መካከል ፈቃደኛ ሆነው በተገኙ 124 የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ላይ ጥናት አካሂዷል፡፡ በቅድመና ድህረትምህርት ፈተና በተሰጣቸውና እኩል ቁጥር በሌላቸው ተጠኝና ጥብቅ ቡድን ተጠቅመው ለሁለት ወራት ያህል ሶስት ዓላማዎችን ነድፈው ለ20 ሰዓታት ተሳታፍዎችን በጽብረቃተኮር መጻፍ ካስተማሩ ቦኋላ ችሎታተኮር ምዘና አካሂደዋል፡፡በጥናት ውጤቱም አዎንታዊ ምላሽ አገኝተዋል፡፡
ለተማሪዎች በቀረበ መጠይቅና ባካሄዱት ምልከታ የተሳታፍዎች ውጤታማነት በተደጋጋሚ መጨመሩንና ፈጣን ለውጥ መኖሩን ያመላከተ ሲሆን በጽብረቃተኮር የመፃፍ ልምምድ ሂደት ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ በአንድ ችሎታ ላይ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡በተጨማሪም ተሳታፍዎች በቡድን መወያየታቸው ግልጽ ያልሆኑላቸን ለመወያየት እንደሚጠቀሙበት አረጋግጠዋል፡፡

በመሆኑም በጽብረቃተኮር ትንተና ሂደት ተሳታፍዎች ግብረ መልስ ማግኘታቸዉ ልምድና ጥሩ ግንዛቤ እንዲያዳብሩ በራስ መተማመናቸውን ይጨምራል፡፡ሆኖም ግን የሰዓት አጠቃቀማቸው ጥሩ አልነበረም በማለት (Boman, 2014) ያብራራሉ፡፡
በአጠቃላይ በአጭሩ በተከለሱና በተተነተኑ ጥናቶች እንደሚታየው  ፅብረቃ ተኮርን ማስተማር የተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ የሚያዳብር መሆኑንና የመፃፍ ትምህርት ፅብረቃ ተኮር ከመፃፍ ትምህርት በተጨማሪ ማህበራዊ እናአዕምሮአዊ እውቀትን ሊያዳብር እንደሚችል በርካታ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

## ምዕራፍሶስት፤የአጠናንዘዴ

ይህ ጥናት የተከናወነው ቅድመፍትነታዊ የምርምር ስልትን መሰረት አድርጎ የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረትምህርት ፈተናን ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡ ከቁጥጥር ውጭ የሚሆኑ ተላውጦችን ለመቆጣጠር የተሳታፍዎችን ችሎታ ለመለካት ያስችል ዘንድ የሁለት ቡድን ጥናት ንድፍ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

### 3.1 የጥናቱ ተሳታፊዎች

ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን በወረ ጅሩ  2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2014 ዓ.ም በ9ኛ ክፍል በሚማሩ 50 ተማሪዎች ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ የተመረጠው በአመች  የእጣ ናሙና ዘዴ ሲሆን

በሌሎች አጎራባች ትምህርት ቤቶች ጥናቱ ቢካሄድ አጥኚው ረጅም ርቀት ተጉዞ ለጥናቱ ተሳተፊዎች ተከታታይ ልምምድ እና ምጋቤ ምላሽ በምሰጥበት ወቅት አጥኚው መደበኛ የማስተማር ስራ ላይ ተፅዕኖ እንዳይፈጥርና መረጃ ለመሰብሰብ ምቹ እንዲሆን በማለት ትምህርት ቤቱ ተመርጧል፡፡ ይህ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት ችግሩ የታየበት እና አንጻራዊ በሆነ መልኩ የመጻፍ መልመጃዎች ሰፊ ሽፋን የሚገኙበት በመሆኑ ነው፡፡

በ2014 ዓ.ም በወረ ጅሩ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካሉት 6 የ9ኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች መካከል እድል ሰጭ የናሙና አወሳሰድ ዘዴዎች ቀላል የእጣናሙና ዘዴን መሰረት በማድረግ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲለዩ ተደርገው 9ኛ A እና የ9ኛ Bክፍሎች ከተመረጡ በኋላ በ9ኛ A ክፍል ለሚማሩ 25 ተማሪዎች እና በ9ኛ B ለሚማሩ 25 ተማሪዎች በአጠቃላይ 50 ተማሪዎች ተመርጧል፡፡ለአሰራር ያመች ዘንድ በአጥኚው ቡድን ሀ፤እና ቡድን ለ በሚል ተሰይመዋል፡፡ከዚያም ቅድመትምህርት በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጎ አማካይ ውጤታቸውና መደበኛ ልይይታቸው ተሳልቶ ቡድን ሀ፣56.46 ቡድን ለ 56.82 ሆኗል፡፡በመሆኑም የሁለቱም ቡድን ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤታቸው ተቀራራቢ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

ከዚህም ባሻገር ሁለቱም ቡድን የትኛው ዘዴ ተግባራዊ እንደሚደረግ የተለዩትም በተራ እጣ ናሙና ስልት ነው፡፡በእጣው መሰረትም 9ኛ A በሙሉ የቁጥጥር ቡድን እየተሰጣቸው በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ልምምድ የማያደርጉ የቁጥጥር ቡድን (control Group) ሲሆን፤9ኛ B በሙሉ የሙከራ ቡድን (Experimental Group) እየተሰጣቸው በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ልምምድ የሚያደርጉ መሆናቸው ተለይቷል፡፡እንዲሁም በጥናቱ የተሳተፉት 50 ተማሪዎች ሳያቋረጡ እስከ መጨረሻው ተሳታፊ መሆናቸው በጥናቱ ውስጣዊ ትክክለኛነት ላይ ተጽዕኖ ሊያደርስ የሚችለውን አቋራጭነት ለመቆጣጠር አስችሏል፡፡

### 3.2 የመረጃመሰብሰቢያመሳሪያዎች

በዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ያገለገሉት ቅድመና ድህረ ትምህርት በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተናዎች ናቸው፡፡

3.2.1 ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች

የጥናቱ ተሳታፊዎች ሁለት ጊዜ ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተናዎችን ተፈትነው ስለ መጻፍ ችሎታቸው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የመጀመሪያው ቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ነው፡፡ የዚህ ፈተና ውጤትም በጥናቱ መነሻ ላይ ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ልምምዱን ከመጀመራቸው በፊት ተመጣጣኝ ውጤት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ውጤት ለሁለቱም ቡድኖች የጥናቱ ቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ውጤታቸው ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

የድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተናው ደግሞ ተማሪዎች ተደጋጋሚ አስረጅ ድርሰት የመጻፍ ልምምድ ካደረጉ በኋላ የተሰጠ ሲሆን አላማውም ሁለቱ የሙከራ ቡድኖች የተለያየ ምላሽ እየተሰጣቸው ድርሰት የመጻፍ ልምምድ በማድረጋቸው ድርሰት በመጻፍ ችሎታቸው ላይ መበላለጥ ስለመታየት አለመታየቱ መረጃ መስጠት ነው፡፡

ፈተናው አንድም ከቅድመ ፈተናው ውጤት ጋር ያለውን ልዩነት ወይም ተመሳሳይነት በሌላ በኩልበሁለቱ ቡድኖች ማለትም በተለያዩ ዘዴዎች አስረጅ ድርሰት የመጻፍ ችሎታን በተለማመዱ ተማሪዎች ውጤት መካከል ሊኖር የሚችልን ልዩነት ለማነጻጸር የተዘጋጀ ነው፡፡

ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችን ለማዘጋጀትም አጥኚው በቅድሚያ 5 ርዕሶችን መርጧል፡፡ርዕሶቹ ሲመረጡም በመረሀ ትምህርቱ መነሻነት የተጠኚ ተማሪዎችን ዳራ/ልምድና የክፍል ደረጃ ከግንዛቤ በማስገባት እንዲሁም የተማሪዎችን የመማሪያ መጽሀፍ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ከነዚም ርዕሶች ውስጥ ለፈተናዎቹ የሚውሉትን ለመለየት በደረጃው ከሚያስተምሩ የአማሪኛ ቋንቋ መምህር ጋር ምክክር ተካሂዷል፡፡ በምክክር ሂደቱም ከአምስቱ ርዕሶች ውስጥ ድርሰት ለመጻፍ አምስቱ ርዕሶች ለፈተና ዝግጅቱ ተመርጠው በደረጃ እንድጠቀሙ ተደርጓል፡፡በመቀጠልም በአብዛኞቹ ተማሪዎች ቅድሚያ የተሰጣቸው ሁለት ተቀራራቢነት አቻነት ያላቸው ርዕሶች ተለይተው በአብዛኞቹ ተማሪዎች የተመረጡና የተለያዩ ባለሙያዎችን እንዲሁም የአማካሪዬን ይሁኔታም ያገኘ ርዕሶች በመሆናቸው ለቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና እንዲያገለግሉ ተደርጓል፡፡ ቅድመናድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ከሙከራ ጥናቱ ቀደም ብሎ ከላይ በተጠቀሱት ባለሙያዎች ግምገማ ተደርጎባቸዋል፡፡እንዲሁም በሙከራ ጥናቱ ወቅትም ከዋናው ጥናት ተሳታፊዎች ጋር አቻነት ያላቸውን ተማሪዎች በመፈተን በዋናው ጥናት ጊዜ ደግሞ ለጥናቱ ተሳታፊዎች በማቅረብ በጥቅሉ ለሁለት ጊዜ ያህል በልዩ ልዩ የስታትስቲክስ ስሌቶች ጭምር ተፈትሸዋል፡፡

ሁለቱን ፈተናዎች ለማረምም (ቅድመናድህረ) ትንታኔያዊ የእርማት ዘዴ ተመርጧል፡፡በተንታኝ ዘዴ የመጻፍ ብቃት ግምገማ የሚመሰረተው በተለያዩ ባህርያት ላይ ነው፡፡ለምሳሌ፤ይዘት አደረጃጀት ፤የቃላት ትስስር ሰዋሰው እና ስርዓተ ነጥብን ለየብቻ ስለሚገመግም ስለ ጽሁፉ ባህሪ ጥቅል መረጃ ይሰጣል፡፡ይህ ዘዴ አስቸጋሪና አድካሚ ተግባር ቢሆንም አስተማማኝ ለሆነ ምዘና ግን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በጥናቱ የመጣውን ለውጥ ወይም ውጤት ለማወቅ ከትምህርቱ በኃላ ተሳታፍዎች የመፃፍ ችሎታ ፈተና ይተነተናል፡፡ በመጨረሻው ፈተና ዓላማ ደግሞ ትምህርቱን ከተማሩ በኃላ በጉልህ የሚታይ የመፃፍ ችሎታ እንዳለ ለማወቅ ነው፡፡

የጥናቱ ተሳታፍዎች በፅብረቃዊተኮር መጻፍ ብልሐት ከተለማመዱ በኃላ በቅድመ ትምህርት ፈተናው የነበረውን ሂደት በጠበቀ መንገድ በተመሳሳይ ፈታኞችና በተመሳሳይ ሰዓት እንዲሁም በተመሳሳይ ክፍል

ተፈትኖዋል፡፡የተሳታፍዎች ፈተና በቅድመ ትምህርት መመዘኛው መሰረት በሁለት የቅድመ ትምህርት ፈተና የፈተና አራሚዎች ከታረመ በኃላ አማካይ ውጤቱ ይመዘገባል፡፡

## 3.3 የማስተማሪያመሳሪያዎች

በዚህ ጥናት ለሁለቱ የሙከራ ቡድኖች የማስተማሪያ መሳሪያ ሆነው ያገለገሉት የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ 2004 ዓ.ም አሻሽሎ ባዘጋጀው የ9ኛ ክፍል መመሪያ መጽሀፍ ውስጥ ለመጻፍ ልምምድ የቀረቡ ይዘቶች ናቸው፡፡በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት የመጻፍ ተግባራት የመጻፍ ልምምዱን ተግባራዊ ለማድረግ የተመረጡበት ምክንያት ሌላ አዲስ የማስተማሪያ መሳሪያው መለያየት ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ ተላውጦዎችን ለመቆጣጠር ታስቦ ነው፡፡ከዚህ አንጻር ለሁለቱ የሙከራ ቡድኖች ሌላ የተለየ የማስተማሪያ መሳሪያ አልተዘጋጀም፡፡

## 3.4. የአጠናንሂደት

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ በአጥኚው ከተዘጋጁ ቦኋላ በተለያዩ ባለሙያዎች ተገምግሟል፡፡በመቀጠል ርዕሶቹን ለተጠኚ ተማሪዎች በማቅረብ ከአንድ ጀምረው እስከ መጨረሻው ድረስ ለጽሁፍ ርዕስነት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በደረጃ እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው፡፡በመቀጠል በአብዘኞቹ ተማሪዎች የተሰጣቸው ሁለት አቻነት ያላቸው ርዕሶች ተለይተው ለቅድመ ትምህርት ፈተናና ለድህረ ትምህርት እንድውሉ ተደረጓል፡፡ ከዚያም ሙከራ ጥናቱ ተካሂዶ ትክክለኛነታቸውና አስተማማኝነታቸው ለማረጋገጥ ነው፡፡ በሙከራ ጥናቱ ወቅትም ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተገኙ ውጤቶችን መነሻ በማድረግ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ በአጥኚው የተወሰነ ማሻሽያ ተደርጎባቸው ለዋናው ጥናት ተዘጋጅቷል፡፡

ከዚያም በሁለቱም ቡድን የሚገኙ ተማሪዎች በጽብረቃተኮር መጻፍ ልምምዱን ከመጀመራቸው በፊት ባሉበት ክፍል 25/6/2014.ዓ.ም ቅድመትምህርት ፈተና ይሰጣል፡፡ በመቀጠል የተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና ሁለት አራሚዎች ታርሞ በነጠላ ልይይት ትንተና ይተነተናል፡፡ በመጨረሻም በቅድመ ትምህርት ፈተናው የሁለቱም ቡድን ተማሪዎች በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤታቸው ይታወቃል፡፡

ከዚያም ቅድመ ትምህርት ፈተናውን ከተፈተኑ ከሁለት ቀናት በኋላ ማለትም 28/6/2014 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 12/08/2014 ዓ.ም ድረስ ሁለቱም ቡድኖች የተለያዩ ጽሁፎች እየተሰጣቸው በስድስት ሳምንታት ውስጥ ለ18 ክፍለ ጊዜያት በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ልምምድ እንድያደጉ ማድረግ ነው፡፡ለዚህም በሙከራው ለሚሳተፉ ለሁለቱም ቡድኖች አጥኚው አንዳንድ ደብተር ወረቀትና እስክሪቢቶ በመስጠት በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ልምምዱ ተግባር ከቁሳቁስ አንጻር ወጪ እንዳያወጡ አድርጋለው፡፡

በመቀጠል ስድስት ሳምንታቱ ከተጠናቀቀ ከሁለቱ ቀናት በኋላ 14/8/2014 ዓ.ም ሁለቱ ቡድኖች በተመሣሣይ ሁኔታ ድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትኗል፡፡በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት መረጃዎች ሲሰበሰቡ

ተመጣጣኝ የጊዜ አጠቃቀሞች ይስተዋላል፡፡ይኸውም ለቅድመ ፈተናው 1.ሰዓት ከ30 ደቅቃ ለድህረ ፈተናው 1.ሰዓት ከ30 ደቅቃ ይጠቀማሉ፡፡ከሁለቱም ቡድኖች መረጃዎች ሲሰበሰቡ አጥኚው በተገኘበት ጊዜና ሁኔታ ነው፡፡

እንዲሁም በመረጃ አሰባሰብ ሂደት እንደ መፈተኛ አካባቢ ድምጽና ረብሻ፣ኩረጃና የጊዜ እጥረት ያሉት በመረጃው ትክክለኛነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔቶችን ለመቆጣጠር አስፈላጊው ጥንቃቄ ማድረግ ነው፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ መረጃዎች የተሰበሰቡበት በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተናዎች እና ለተማሪዎች የተዘጋጀ ጥያቄዎች አማካኝነት እንደሆነ ቀደም ሲል ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

በዚህ መሰረት የጥናቱን ተሳታፊ ሁለት ቡድኖች አቻነት ለማወቅ አገልግሎት ላይ የዋለው ቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ለየቡድኖቹ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡

በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በነጠላ ልይይት ትንተና ፍተሻ ተካሂዷል፡፡የነጠላ ልይይት ትንተና የተካሄደውም እሙኖቹ ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ በኮልሞኖቭ-ስሚኒቭ ቴስትና በተያያዥ አምድ ግራፍ የውጤት ስርጭት ወጥነቱ በሌቪንስ የልይይቶች ተመጣጣኝነት መፈተሻ ቴስት የአማካይ ውጤቶች የልይይት መጠን እኩልነት ከተረጋገጠ በኋላ ነው፡፡እንዲሁም ቡድኖቹ በድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የነጠላ ልይይት ትንተና ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

## ምዕራፍ አራት፣ የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ቀደም ሲል በምዕራፍ ሶስት የጥናቱን ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አዘገጃጀታቸውን እና የሚተነተኑባቸውን ዘዴዎች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡እንዲሁም ለዋናው ጥናት በግብዓትነት ሊያገለግሉ የሚችሉ መሰረታዊ ጉዳዮችን ለመለየት የቅድመ ሙከራዊ ጥናቱን ከተገኙ ተመክሮዎች በመነሳት የዋና ጥናቱ የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

### 4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና

የዋና ጥናቱ የውጤት ትንተና ከመደረጉ በፊት በቅድመ እና በድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተናዎች የአራሚዎች የስምምነት ደረጃ በክሮንባኽ አልፋ ስሌት እንዲሰላ ተደርጓል፡፡ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥም ፈተናዎቹ በሁለት አራሚዎች ሲታረሙ የተገኙትን የክሮንባኽ አልፋ ውጤቶች የሚያሳይ ነው፡፡እንዲሁም በሁሉም ትንታኔዎች ለስታትስቲካዊ ስሌቶች ፍተሻ የጉልነት ደረጃው 0.05 እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በሰንጠረዥ 4.1 የቅድመና የድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች የአራሚዎች የስምምነት ደረጃ በክሮንባኽ

| ቡድኖች | ቅድመ ፈተና | ድህረ ፈተና |
|---|---|---|
| ቡድን ሀ | 0.842 | 0.893 |
| ቡድን ለ | 0.868 | 0.894 |

ሰንጠረዥ 4.1 በቅድመና በድህረ ትምህረት ፈተና በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን የሁለቱን አራሚዎች የስምምነት ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃም መረዳት እንደሚቻለው በቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህር በሁለቱ አራሚዎች መካከል ያለው የስምምነት ደረጃ በቅደም ተከተል ቡድን ሀ 0.842 ቡድን ለ 0.868 የክሮንባኽ አልፋ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡እንዲሁም በድህረ ትምህርት ፈተና ያለውን የስምምነት ደረጃ በቅደም ተከተል ቡድን ሀ 0.893 እና ቡድን ለ 0.894 አስተማማኝነት አሳይቷል፡፡

በሁለቱም ፈተናዎች (በቅድመ እና በድህረ ትምህረት ፈተና) የተገኙትን የክሮንባኽ አልፋ ውጤቶች የሚጠቁሙት በሁለቱም ውስጥ ያለው የአራሚዎች የስምምነት ደረጃ ከፍተኛ (> 0.005) እንደሆነ ነው፡፡

በሌላ በኩል የአራሚዎች የስምምነት ደረጃ እንዲፈተሽ ከተደረገ በኋላ የቅድመና የድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና የመረጃ ስርጭት ወጥነት እና የልይይት እኩሌታ እንዲፈተሽ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥም የሚያሳየው የቅድመ ትምህርትን የድህረ ትምህረት ፈተናውን የመረጃ ስርጭት ወጥነት ደረጃን ነው፡፡

ሰንጠረዥ 4.2 የሙከራ ቡድኖቹ ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ የቅድመ ፈተናና የድህረ ትምህረት ፈተና የመረጃ ስርጭት ወጥነት

| ቡድኖች | ቅድመ ትምህርት ፈተና<br>ድህረ ትምህርት ፈተና | የመረጃ ስርጭት ወጥነት ደረጃ የሚያሳይ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | Statistic | Df | Sig |
| ቡድን ሀ | ቅድመ ፈተና | 0.054 | 25 | 0.200 |
| | ድህረ ፈተና | 0.066 | 25 | 0.200 |
| ቡድን ለ | ቅድመ ፈተና | 0.090 | 25 | 0.200 |
| | ድህረ ፈተና | 0.069 | 25 | 0.200 |

ሰንጠረዥ 4.2 ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ በቅድመ ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን የመረጃ ስርጭት ወጥነት ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃም መረዳት እንደሚቻለው በቅድመ እና በድህረ ትምህረት ፈተና ቡድን ሀ እና ቡድን ለ ተመሳሳይ የጉልህነት ውጤት (0.200) አስመዝግበዋል፡፡በመሆኑም የተመዘገቡት የጉልህነት ውጤቶች ከ 0.05 በላይ መሆናቸው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የመረጃ ስርጭት ወጥነት እንዳለው ሊያመላክት ችሏል፡፡

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ የቅድመ እና የድህረ ትምህርት ፈተና የመረጃ ስርጭት ወጥነትን ለማሳየት ተችሏል፡፡ውጤቱም በሰንጠረዥ 4.3 እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ሰንጠረዥ 4.3 የሙከራ ቡድኖቹ የቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ፡፡

| ቡድኖች | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የአማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|
| ቡድን ሀ | 25 | 56.46 | 5.4 | 0.78 |
| ቡድን ለ | 25 | 56.82 | 4.74 | 0.7 |

ሰንጠረዥ 4.3 ቡድኖቹን የቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡የሁለቱ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች በቅደም ተከተል ቡድን ሀ 56.46 እና ቡድን ለ 56.82 ሆኗል፡፡በእነዚህ ሁለት ቡድኖች መካከል አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡

ይኸውም ቡድን ለ ከቡድን ሀ በ0.36 አማካይ ውጤት በልጦ ታይቷል፡፡እንዲሁም የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና የመደበኛ ልይይት ውጤቶቹም በቅድም ተከተል ቡድን ሀ.5.4፤ቡድን ለ 4.74 ሆኗል፡፡ይህም የሁለቱም ቡድኖች ቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ የወጥነት ባህሪ የሚታይበት ወይም ተቀራራቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በሰንጠረዥ 4.3 እንደተመለከተው የቡድን ለ ተማሪዎች ከቡድን ሀ በ 0.36 አማካይ ውጤት ልዩነት በልጦ ታይቷል፡፡በመካከላቸው ያለው ልዩነት ጉልህ መሆን/አለመሆኑን ለማረጋገጥ ግን ድምዳሜያዊ ስታትቲክስን መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሰንጠረዥ 4.4 እንደተመለከተው የነጠላ ልይይት ትንተና ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሰንጠረዥ 4.4 የሙከራ ቡድኖቹ የቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች ልዩነት በነጠላ ልይይት ትንተና

| ቡድኖች | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት (SD) | የነጻነት ደረጃ(df) | የልይይት ዋጋ(F) | ጉልህነት (sig) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን ሀ | 25 | 56.46 | 5.4 | 2.1656 | 0.082 | 0.922 |
| ቡድን ለ | 25 | 56.82 | 4.74 | | | |

$p>0.05$

ሰንጠረዥ 4.4 ቡድኖቹ በቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና አመካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡መረጃው በነጠላ ልይይት ትንተና ተሰልቶ በሁለቱም ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ ($F=0.082$, $df=2.16$ $p=0.922$) አሳይቷል፡፡ይህም ሁለቱም የሙከራ ቡድኑ የተለያዩ ጽሁፎችን እየተሰጠ ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ልምምድ ከማድረጋቸው በፊት በቅድመ ትምህርት በመጻፍ ችሎታ ፈተና ላይ ጉልህ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

በዚህ ሁኔታ በቅድመ ትምህርቱ ሁለቱ የሙከራ ቡድን ተማሪዎችየመጻፍ ችሎታቸው ላይ የጎላ ልዩነት አለመኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ ሁለቱ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በጽብረቃተኮር መጻፍ እየተሰጧቸው የመጻፍ ልምምድ ሲያደርጉ ቆይተው ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ተፈትነዋል፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ የመጀመሪያ መሰረታዊ ጥያቄ ከሁለቱ የሙከራ ቡድኑ በተማሪዎች የሙከራ ቡድኖች የተማሪዎች ጽብረቃተኮር

መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር/አለመኖሩን ለማረጋገጥ ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስን መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሰንጠረዥ 4.5 እንደሚከተለው በነጠላ ልይይት ትንተና ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.5 የሙከራ ቡድኖቹ የድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶች ልዩነት ትንተና ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

| ቡድኖች | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት (SD) | የነጻነት ደረጃ(df) | የልይይት ዋጋ(F) | ጉልህነት (sig) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን ሀ | 25 | 58.44 | 7.05 | 2.135 | 05.997 | 0.003 |
| ቡድን ለ | 25 | 58.47 | 5.28 | | | |

ሰንጠረዥ 4.5 በሙከራ ቡድኖቹ ድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት እንዳለ ያሳያል፡፡መረጃው በነጠላ ልይይት ትንተና ተሰልቶ በሁለቱ የሙከራ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (F=5.997,df=2.135, p=0.003) አሳይቷል፡፡ይህም የሚያሳየው በተለያዩ ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ልምምድ ያደረጉና ያላደረጉ ቡድኖች መካከል በድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ በመጻፍ ችሎታቸው ላይ ጉልህ ልዩነት መኖሩን ነው፡፡

ይህንን ይበልጥ ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ቡድን በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት በጽብረቃተኮር መጻፍ በመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶች በማነጻጸር መፈተሽ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በጽብረቃተኮር መጻፍ እየተሰጣቸው የመጻፍ ልምምድ ያደረጉ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት በመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር/አለመኖሩን ለመፈተሽ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 4.6 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.6 የቡድን ሀ ቅድመና ድህረ ትምህርት በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

| ፈተና | ናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የአማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 25 | 56.46 | 5.5 | 0.78 |
| ድህረፈተና | 25 | 58.44 | 7.05 | 1.02 |

ሰንጠረዥ 4.6 የቡድን ሀ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርትጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ያስመዘገቧቸውን አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃም መረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎች ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተመዘገበው አማካይ ውጤት 56.46 ሲሆን

መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 5.4 ነው፡፡እነዚሁ ተማሪዎች ድህረ ትምህርት ፈተናውን ተፈትነው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 58.44 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ 7.05 ነው፡፡ከዚህ አንጻር በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ የተገኙት አማካይ ውጤቶች ሲታዩ በድህረ ፈተና የተመዘገበው በቅድመ ፈተና ከተመዘገበው ጋር ሲነጻጸር በ1.99 አማካይ ውጤት ብልጫ አሳይቷል፡፡ይህ ውጤትም ጉልህ መሆር/ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስን መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሰንጠረዥ 4.7 እንደሚከተለው በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.7 በቡድን ሀ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተና መካከል የአማካይ ውጤቶች ልዩነት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት

| ፈተና | ናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 25 | 56.46 | 5.4 | 1.509 | 47 | 0.138 |
| ድህረ ፈተና | 25 | 58.44 | 7.05 | | | |

ሰንጠረዥ 4.7 የቡድን ሀ ተማሪዎች በቅድመ ትምህረትና በድህረ ትምህርት በመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡መረጃው በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመ ትምህርት ፈተናና በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት (t (47)=1.509) p=0.138) አለመኖሩን ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ ያመላክታል፡፡ይህም የሚያሣየው ጽብረቃተኮር መጻፍ እየተሰጣቸው የመጻፍ ልምምድ ያደረጉ

ተማሪዎች በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት በመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡

የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም ጽብረቃተኮር መጻፍ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል አዎንታዊ ውጤት እንደለው አሳይቷል፡፡በተመሳሳይ ጽብረቃተኮር መጻፍ እየተሰጣቸው የመጻፍ ልምምድ ያደረጉ ተማሪዎች በቅድመና በድህረ ትምህርት በመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር/አለመኖሩን ለመፈተሽ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተትኗል፡፡

ውጤቱም ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 4.8 ተመልክቷል፡፡የቡድን ለ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና መካከል ያለው የአማካይ ውጤቶች ልዩነት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት

| ፈተና | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የአማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 25 | 56.82 | 4.74 | 0.7 |
| ድህረ ፈተና | 25 | 58.47 | 5.28 | 0.78 |

ሰንጠረዥ 4.8 የቡድን ለ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ በመጻፍ ችሎታ ፈተና ያስመዘገቧቸውን አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሣያል፡፡በሰንጠረዡ ከሰፈረው መረጃም መረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎች ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ በቅድመ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡትን አማካይ ውጤት 56.82 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 4.74 ሆኗል፡፡እነዚሁ ተማሪዎች ድህረ ፈተናውን ተፈትነው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 58.47 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 5.28 ሆኗል ከዚህ አንጻር በቅድመና በድህረ ፈተናዎቹ የተገኙት አማካይ ውጤት ብላጫ አሳይቷል፡፡ስለዚህ በሁለቱ ፈተናዎች (ቅድመና ድህረ) መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስን መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሰንጠረዥ 4.9 እንደሚከተለው የጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

በቡድን ለ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና መካካል ያለው የአማካይ ውጤቶች ልዩነት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት

| ፈተና | ናሙና | አማካይ.ውጤት | መ.ደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 25 | 56.82 | 4.74 | 1.709 | 45 | 0.095 |
| ድህረ ፈተና | 25 | 58.47 | 5.28 | | | |

ሰንጠረዥ 4.9 የቡድን ለ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ በመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ መረጃውም በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል አለመኖሩን ውጤቱ (t (45) =1.706, P=0.095) አመላክቷል፡፡

ይህም የሚያሳየው ጽብረቃተኮር መጻፍ እየተሰጣቸው የመጻፍ ልምምድ ያደረጉ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት በመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶች መካካል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡

የትንተናው ውጤት መሰረት በማድረግም ጽብረቃተኮር መጻፍ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል አዎንታዊ ውጤት እንዳለው ተረጋግጧል፡፡እንዲሁም ጽብረቃተኮር መጻፍ ከመጻፍ ልምምዱ በኋላ የሙከራ ቡድኖቹ ባላቸው አመለካከት መካከል ጉልህ ልዩነት  አለቸው የሚለው ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለውን አስተዋፅኦ መፈተሽ ነበር፡፡ለዚህም የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡በመሆኑም የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይህም በፅብረቃተኮር መፃፍና በመፃፍ ችሎታ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን አመላክቷል፡፡በመሆኑም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ

ትምህርት መማር የመፃፍ ችሎታ ያዳብራል፤የሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ ይችላል፡፡ምክንያቱም በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች በፅብረቃተኮር መፃፍ መፃፍን በመማራቸው የመፃፍ ችሎታ ፈተናው ውጤት ተፈትሿል፡፡በዚህ መሰረት በፅብረቃተኮር መጻፍ መደምደሚያ ላይ የመፃፍ ትምህርትን መማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ ጠቀሜታ እንዳለው ያሳየው ይህ የጥናት ውጤት በጥናታቸው መፃፍ ያለፅብረቃተኮር መጻፍ አጋዥነት ስኬታማ ሊሆን እንደማይችል ካመላከቱት Burton.J. እና ሌሎቹ (2009) እንዲሁም በፅብረቃተኮር መፃፍ ትምህርትን መማር የመፃፍ ችሎታን ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው በጥናት ውጤታቸው ካመላከቱት karoli Rojers (2002) Trekking (2002) B.N.sen (2010) Roos,N, (2011) Boman (2014) ጥናቶች ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአንፃሩ ደግሞ ይህ ጥናት ከLaura hulick (Kiya) ጥናት ጋር ተቃርኗል፡፡በፅብረቃ ተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ በማሳደግ ረገድ አስተዋጽኦ አለው የሚል ዓላማ ነበር፡፡ለዚህም የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ለመረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል፡፡በዚህም መሰረት በቅድመና ድህረ ትምህርት የመፃፍ ችሎታ የፈተናዎች አማካይ ውጤት መካከል በስታትክስቲካስ ጉልህ ልዩነትአለመኖሩን ያሳያል፡፡ይህም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርትና በመፃፍ ችሎታ መካከል አዎንታዊ እንዳለ አመላክተዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ መማር ተሻሽሏል፡፡የሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ ይችላል፡፡በመሆኑም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርት መማር የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ከማጎልበት አኳያ አዎንታዊ ሚና እንዳለው ያሳየው ይህ ጥናት ከRoos N (2011) ጥናት ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡
በሌላ በኩል ደግሞ በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ መመርመር ሲሆን ለዚህም የጥናቱ ተሳታፊዎች በልምምድ ሂደት የፃፉት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ክትትል ከተደረገ በኋላ የተሰበሰበ መረጃ በነጠላ ልይይት ተተንትኗል፡፡ስለዚህ በፅብረቃተኮር መፃፍና በመጻፍ ችሎታ መካከል ቀጥተኛ ግንኙኝነት እንደለ ያመላክታል፡፡ይህም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርት መማር መፃፍ ችሎታ መረዳትና በተገቢ መንገድ የመተግበር ችሎታን ያዳብራል፡፡የሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ ይችላል፡፡

በመሆኑም በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች በልምምድ ሂደት የፅብረቃተኮር መጻፍ ቀጣይነቱን በማቀድና በተማሩት አውድ መካከል ያለውን መስተጋብር በማብራራትና በቀጣይነቱ የሚከተለውን ትርጉም በመገንዘብ ትኩረት የመስጠት ችሎታ ማጎልበት ችለዋል፡፡
ይህም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርት መማር የመጻፍ ችሎታን የመረዳትና በፅሁፍ ውስጥ የመተግበር ችሎታን ከማጎልበት አኳያ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዳለ ያመላከተው ይህ ጥናት Noos N (2011) Sen.B.A,moon.J (2004) Lind.E.Maritn Sherliziaker (2009) የጥናት ውጤት ጋር ተደጋጋፊ ሲሆን ከLaura hulick(kiya) ጥናት ጋር የሚቃረን ቢሆንም Laura hulick (kiya) በጥናታቸው እንዲመለሱ ለጠቆሟቸው ጥያቄዎች አመላካች ሊሆን የሚችል ውጤት እንዳለ ይህ ጥናት አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት በተገኘው ውጤት ትንተና በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርት መማር የመፃፍ ችሎታን ከማደበር አኳያ ያለው አዎንታዊ አስተዋፅኦ የጎላ ነው፡፡እንዲሁም በፅብረቃተኮር መፃፍን መማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ከማዳበሩ ጎን ለጎን የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎተ ያጎለብታል፡፡በተመሳሳይ በፅብረቃተኮር መፃፍ መፃፍን መማር የፅብረቃተኮር መፃፍ የመጻፍ ችሎታን ያዳብራል ወደሚል ድምዳሜ ሊደርስ ይችላል፡፡

## ምዕራፍአምስት፤ ማጠቃለያ መደምደሚያና መፍተሄ ሀሳቦች

### 5፤1 ማጠቃለያ

በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታን በማሳደግ ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ በዚህ ጥናት ሊመለስ የታሰበ ጥያቄ የሚከተሉው ነው፡፡

1 በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታን በማሳደግ ረገድ አስተዋጽኦ አለውን?

የጥናቱ አካባቢ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን ለታ ስቡ ወረዳ የሚገኘው የወረ ጅሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ነው፡፡ ትምህርትቤቱ በዓላማ ተኮር የእጣ ናሙና ተመርጧል፡፡ በዚሁ ትምህርትቤት በ2014 ዓ.ም በትምህርትቤቱ ካሉት 8 የ9ኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች መካከል በእድል ሰጭ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ የ9ኛA እና የ9ኛB ክፍል ተመርጧል፡፡ በመቀጠል በክፍሉ ለሚማሩ 50 ተማሪዎች በተሰጠ በቅድመትምህርት ፈተናና በድህረ ትምህርት ፈተና 50 ተማሪዎች ጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡የአጠናን ዘዴው ፍትነታዊ (የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረ) ሲሆን ለጥናቱ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት እንዲችል ፈተናዎች ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሏል፡፡

ቅድመትምህርት ፈተናው በጥናቱ አማካሪና በሌሎች ባለሙያዎች ማስተካከያ ተሰጥቶበትና በሙከራ ጥናት ተፈትሾ አስተማማኝ በመሆኑ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡በመቀጠል ቅድመ ፈተናው የጥናቱ ተሳታፊዎችን ለመምረጥና የጥናቱ ተሳታፊዎች ከመነሻ የነበራቸውን የመፃፍ ችሎታ ለማወቅ አገልግሏል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች Rolf እና ሌሎች (2011) አሻሽለው ባዘጋጁት ሞዴል መነሻነት በፅብረቃተኮር መፃፍ ለማለማመድ የሚያስችል የተሳታፊዎችን የትምህርት ደረጃና መረሃትምህርቱን መሰረት ያደረገ ከተማሪዎች የአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ትምህርት ማስተማር እንዲመች በጥቂቱ መሻሻል ተደርጎ በተዘጋጀ በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ ትምህርት ማስተማሪያ ማሳሪያዎች ስድስት ሳምንታት ተለማምደዋል፡፡

ከዚያም በቅድመ ትምህርት ፈተናው የነበረውን ሂደት በጠበቀ መንገድ በተመሳሳይ ፈታኞችና በተመሳሳይ ፈተና በድህረ ትምህርት ሰዓት እንዲሁም በተመሳሳይ ክፍል ከቅድመ ፈተናው ተመሳሳይ ፈተና በድህረ ትምህርት ፈተናው ተግባራዊ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ የማስተማሪያ መሳሪያ ነው፡፡አገልግሎቱም የጥናቱ ተሳታፍዎች በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ ትምህርት በመማራቸው በመጻፍ ችሎታው ላይ ያለውን አስተዋጽኦ ለመመርመር ነው፡፡

ለዚህም የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ 2004 ዓ.ም አሻሽሎ ባዘጋጀው የ9ኛ ክፍል መመሪያ መጽሀፍ ውስጥ ለመጻፍ ልምምድ የቀረቡ ይዘቶችን ለጥናቱ በሚመች መልኩ ተሸሽሎ በጥናቱ አማካሪ ማስተካከያ ተሰጥቶበታል፡፡ ቀጥሎም በዋናው ጥናት ላይ ተግባራዊ ከመደረጉ በፍት በሙከራ ጥናት ፓይለት ስተዲ/አስተማማኝነቱ ተረጋግጦ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ፈተናው በተሳታፍዎች የተሰራው በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ነው፡፡

በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ ትምህርት መማር ሂደት የፅብረቃተኮር መፃፍ የመጻፍ ችሎታን ለመመርመር የተሳታፊ ተማሪዎች የመጻፍ ስራ በአጥኝውና ስልጠና በወሰደ አንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህር ተከታታይ ክትትል ለ18 ቀናት መረጃ ተሰብስበዋል፡፡በአጠቃላይ በፈተናዎች የተሰበሰበ መረጃ በገላጭና ድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡በቅድመ ትምህርት ፈተናና በድህረ ትምህርት ፈተና የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን ነጠላ ልይይት ትንተና አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡በዚህ መሰረት ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በልጦ ተገኝቷል፡፡በአማካይ ውጤቶች መካከል የጎላ ($P<0.05$ )ልዩነት መኖሩንም በስታትስቲክስ የተገኘው ውጤት አመላክቷል፡፡ከተገኘው ውጤት በመነሳት በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርትን መማር የመፃፍ ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለው አስተዋፅኦ የጎላ ነው፡፡

በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተና ተማሪዎችን የመጻፍ ስራ ተሰብስበው መረጃ ነጠላ ልይይት ትንተና ተተንትኖዋል፡፡በዚህ መሰረት በቅድመና በድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ጽሁፍ አማካይነት ውጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉሊህ ($p<0.05$) ልዩነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ስለዚህ በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ትምህርትን መማር የመጻፍ ችሎታን ከማደሳደግ አኳያ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው አመላክተዋል፡፡
በፅብረቃተኮር  መፃፍ ሂደት ከጥናቱ ተሳታፊዎች ፈተናዎች የተሰበሰበው መረጃ በገላጭ ስታትክስቲክ ተተንትኗል፡፡በዚም መሰረት በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርት መማር የፅብረቃተኮር መጻፍ የመረዳትና በተገቢ መንገድ የመጻፍ ችሎታን ያዳብራል፡፡ይህም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርት መማር ሂደት በተከታታይ ልምምድ የተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ እድገት ላይ አዎንታዊነት  እንዳለው ሊያመላክት ይችላል፡፡
በአጠቃላይ በዚህ ጥናት በተገኘው ውጤት በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ ትምህርት መማር የመፃፍ ችሎታን ያዳብራል፡፡እንዲሁም የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታን ያሻሽላል፡፡ በተጨማሪም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመጻፍ ችሎታን መረዳትና የመተግበር ችሎታን ያሳድጋል፡፡በዚህ መሰረት የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማጎልበት በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ ትምህርትን መማር ውጤታማ  ሊያደርግ እንደሚችል የተገኘ ውጤት አመላክተዋል፡፡

## 5.2.መደምደሚያ.

የጥናትውጤቱንና ማብራሪያውን መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ተደርሷል፡፡
1.በጥናት ውጤቱ መሰረት በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ ትምህርትን መማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ በማሳደግ ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ጉልህ ነው፡፡ ይህም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ ትምህርትን መማር የመፃፍ ችሎታን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ወደሚል መደምደሚያ ያደርሳል፡፡
በመቀጠልም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታን መማር በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ላይ ያለው  አዎንታዊ ነው፡፡ይህም በፅብረቃተኮር መፃፍ የመጻፍ ትምህርትን መማር የመፃፍ ችሎታን ከማጎልበት አኳያ አዎንታዊ አስተዋፅኦ አለው፡፡

በዚህ መሰረት በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርት መማርና በፅብረቃተኮር መጻፍ መፃፍ ችሎታን መረዳትና በተገቢ መንገድ መተግበር መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ታይቷል፡፡ይህም በተከታታይ ፅብረቃተኮር መጻፍ ሂደት የፅብረቃተኮር መፃፍ ደረጃዎችን ተከትሎ የመፃፍ ትምህርት መማር የፅብረቃተኮር መፃፍ ችሎታን ያደብራል፡፡

## 5.3 መፍትሔ

የጥናት ውጤቱን መሰረት በማድረግ በፅብረቃተኮር መጻፍ የመፃፍ ትምህርት የመፃፍ ችሎታን ለማዳበር ያለውን አስተዋፅኦ በሚመለከት የተደረሰባቸውን ውጤቶች ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል የሚከተሉት የመፍትሔ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

1.ጥናቱ በፅብረቃተኮር መፃፍ መፃፍ ችሎታን እንደሚያዳብር አመላክቷል፡፡ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ችሎታን ሲያስተምሩ ተማሪዎች ከቀደመ ልምዳቸው በመነሳት እንዲገልፁ በተፈጠረው አውድ የተሰማቸውን ስሜት እንዲተረጉሙ፤የጉዳዩን ጥቅምና ጉዳት እንዲገመግሙ ከተፈጠረው ጉዳይ ተነስተው ያከናወኑትን ጠቃሚና ጎጅ ተግባር እንዲተነትኑ ከርዕሰ ጉዳዩ የተገኘውን እውቀት ገልፀው እንዲደመድሙና ቀጣይ ተግባራቸውን እንዲያቅዱ የሚያግዙ አሃዶችን በመጠቀም ፅብረቃተኮር መፃፍን ተግባራዊ ቢያደርጉ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ከማሻሻል በተጨማሪ የተማሪዎችን መፃፍ የመማር ፍላጎት ሊጨምር ይችላል፡፡የጥናት ውጤቱ በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርትን መማር የመፃፍ ፍላጎትን እንደሚነሳሳ አሳይቷል፡፡

በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርትን ለማስተማር እንዲያስችላቸው፤ለተማሪዎቻቸው የፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ችሎታ የተለያዩ ሞደል በመስራትና በማሳየት በልምምድ ሂደት ድጋፍ በማድረግና ስራቸውን ገምግሞ ተከታታይ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ስለፅብረቃተኮር መፃፍ ምንነትና አተገባበር በትግበራ ደረጃዎች ተግባራዊነቱን በማመላከትና ግንዛቤ በመፍጠር በመፃፍ ትምህርት ልምምድ ወቅት በፅብረቃተኮር መፃፍ የመፃፍ ትምህርትን ተግባራዊ ቢያደርጉት የተማሪዎችን የመጻፍ ቸሎታ ከማነሳሳት በተጨማሪ የመፃፍ ችሎታንም ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል፡፡በፅብረቃተኮር መፃፍ ትምህርት መፃፍ ችሎታንን ማስተማር ከተማሪዎች የመማር ስልት አንፃር ጥናቶች ቢጠና ተማሪዎች በመማር ሂደት ንድፈ ሀሳብን ወደተግባር ለመቀየር የሚችሉበትን መንገድ በማመላከት ረገድ ለተማሪዎችና ለመምህራን ጥሩ ግንዛቤ ሊገኝ ይችላል፡፡

## ዋቢዎች

.ማረው ዓለሙ፡ ፡ 1995፡ ፡ በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፡ ፡ አዲስ አበባ፤ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡ ፡

Argyris,c. & schon, D.1974, Theory in practice; increasing professional Effectiveness, Jossey-Bass, San Francisco

Andrusyszyn, M.A.and Davie,L1997. ''Facilitating Reflection through interactive; Journal Writing in an online Graduate course;AQualitative study in Journal of Distance Education.

BOman, J.(2014) Does Reflective writing Enhance Training/An Evaluation ofaskill-based Teaching Assistance training Program;mount Royal university.

Burton, J.(2009) Reflective writing away to life long teacher learning United State of America.

Chomsky, N.(1976) Reflections on Language (London,Fontana)

Dewey, J. 1933 How we Think; Arestatement of The relation of Reflective Thinking in the Educative process,D.c. Health,New York.

Finlay, L.(2008). Reflecting on Reflective Practice: (www.open.ac-uk/../Finlay (2008), Reflective.Dipcot.Reflective practice.PBP.By, L.Finlay (.2008) Lind.

Gibbs G, (1988) Learning by doing Aguide to teaching and iearning methods oxford further Education unit,oxford peterlia;learning support tutor.Disability

Advisory service; KCL.

Goldberg.N.(1993) Reflective practice for continuous learning long,Quiet highway;workingup in America,2006 by corwin press.

Hillocks, Jr., George.Teaching Writing as Reflective Practice.NY;TCP,1995 Print.

Juliana cuau,Gary,cheng.2012.Developing Chinese student`Reflective second Language Learning skille in higher Education;Association of Gazi foreign Language Teaching.All rights reserve,ISSN;2146-1732

kolb.D.A (1984) Experential Learning; Experience as a source of learing and Development.

Kolb, D.& Fry,R.1975,Towards and Applied theory of experientioal Learning,in Theories of Group processes,ed.c. cooper John wiley & sons,London>

Linda,E.Martin and Shirley Thacker.(2009).Teaching the writing process in priglary Grades one Teachers Approach.

Lucas, p.2012. Critical reflection what do we realiy mean? Auckaland university of Technology (and PhD student Deakin University).

Linda,daring,Hammond,kim Austin.suznne orcutt and Jim Ross 2001 The Learing classroom;Theorning in to practice A Telecqurse for Teacher Education and professional Development Stanford university school Education.

Moon.J.A.(2004) Ahand book of reflective and experiential Learning;Theory and Practice.Newyorc.NY Routiedge.

Moon.J.1999, Learning Journals,AHand book for Academics,students and professiona Develoment,Kogan page,London.

Racher.ong.n.d.The role of reflection in student learning.a study of its effectiveness in complementing problem-based learning environments.www.myrp.sgiced!–research/…/role-of-reflecttion-in –student-learning.pdf.According to Andurusyszyn.(1997.2)

Richards,Jack c.1990.The teachers as self-observer.in jacks c.Richards The Language Teaching matrix.

Ross.N (2o11) Reflective Writing an Approach to Development critical Thinking and proficient writing.

Shoon,D.1987, Educating the Reflective practitioner,Jossey-Bass.San Francisco.

Sen.B.A.(2010)Reflective Writing;AManagement skill Library Management 3(1-2) P90-93 http;//dx.dol.org/10.01108/0143512101101242

Stern;H.H.Fundamental concepts of Language Teaching Oxford university press.

Schon,D.(1983) The Refiective Practive; How Professionals Think in Action.New York;Basic books.

Tyler;R.1949.Basic principles of curriculum and instruction,university of Chicago press.

Watton,p.collings.moon,J.2001.Reflective writing-Guidance Notes For students.Reflective practice and writing;aGuide to Getting started www.alia.org.au/sities/..JEWLS project;www. Jewels.org.uk National centere for work Experience ww.nowe.com.

Terry king 2002 Development of student skills in Reflective writing university of Portsmouth,kingdom.

Williams,K.Woolliams,M.J.(2o12).ReflectiveWriting.Basingstoke;Palgrave Macmillian.

Williams. (2009).The Reflective Model of Intrculral competency Amultidimensia Nal.Qualitative Approach the study abroad assessment tracy rundstro M.Texas Christian university.

Zeicher,K.M.Liston,D.P(2014) Reflective Teaching;An introduction Routledge-New Zeicher,M.(1981)Reflective Teaching and fild based experience,inter change,12(4),1-22

zeicher,Kenneth M.and Daniel P.Liston(1985).varieties of discourse in conferences Teaching and Teacher Education,1,2 (1985),55-174.print.

## አባሪዎች

አባሪ ሀ የቅድመ ፈተና

የቅድመ  ትምህርት ፈተና እና ለድህረ ትምህርት ፈተና የሚያገለግሉ ርዕሶችን ለመምረጥ ለተጠኚ ተማሪዎች ቀርበው በደረጃ የተመረጡ ርዕሶች

**ለዋናው ጥናት ለቅድመትምህርት የቀረበ የመጻፍ ችሎታን የሚያዳብር ፈተና**

በወረ ጅሩ ሁለተኛ ትምህርትቤት 9ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ለዋናው ጥናት የቀረበ ቅድመ ፈተና

ውድ ተማሪዎች የዚህ ጥያቄ ዋና ዓላማ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን በፅብረቃተኮር መፃፍን ማስተማር የመፃፍ ችሎታን በማሳደግ ረገድ ያለው አስተዋፅኦ በሚል ርዕስ ለሚጠና ጥናት መረጃ ለማግኘት ነው፡፡

እናም የዚህን ጥናት አላማ ማሳካት የሚቻለው እናንተ የምትጠየቁትን ጥያቄ በትክክል መመለስ ስትችሉ ብቻ ነው፡፡የፈተናው ውጤትም በተመራማሪው ብቻ በሚስጥር ይይዛል፡፡ለምታደርጉት ሙሉ ትብብርም አጥኚው ልባዊ ምስጋና ያቀርባል፡፡

ሀ. ስም አይፃፍም፡፡

ለ.የምትጽፈው(ፊ) ጊዜያዊ የመለያ ኮድ ቁጥሩን ብቻ ነው፡፡

አጠቃላይ መመሪያ

ይህ ፈተና የመፃፍ ችሎታን ለመለካት የቀረቡ ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን የተለያዩ የመጻፍ ፈተናዎችን ይዞዋል፡፡ተግባር አንድ፤በአንድ ድርሰት በትረካው የተገለጹት ድርጊት የተከናወኑት የት እንደሆነ መጻፍና በትረካው የተከናወኑትን ድርጊቶች በጊዜ ቅደም ተከተል በአጭር በአጭሩ ዘርዘሮ መጻፍ ትረካውን የተረከልን ማን እንደሆነ መግለጽ

ተግባር ሁለት፤በተሰጠ አረፍተ ነገር መነሻነት ምንባቡን አሳጥሮ አንቀፅ መፃፍና  በአስረጂ ድርሰት በተሰጠን ርዕስ አንቀጽ መጻፍ ናቸው፡፡

ፈተናውን ሰርቶ ለመጠናቀቅ 2.00 ተፈቅዶዋል፡፡በአጠቃላይ ከ100% የሚታረም ሲሆን በየጥያቄዎቹ መጨረሻ የእያንዳንዱ ውጤት ይገኛል፤መልሶቻቸውን በመልስ መስጫ ወረቀቶች ላይ ፃፉ፡፡

**ትዕዛዝ አንድ ምንባብን አሳጥሮ አንቀጽ መጻፍ**

1.1 ተግባር፤ አንድ

"አንድ ትልቅ ጦርነት ሲካሄድ ተካፋይ የነበረው አንድ ፈሪ ወታደር ነበር፡፡በጦርነቱ አብረውት የተሰለፉ ጓደኞቹ ደረታቸውን ለጥይት ሰጥተው በጀግንነት ተዋጉ፤እየተመቱም አንዳቸው በአንዳቸው ላይ እየተደራረቡ ወደቁ፡፡ይህንን ያየው ቡቡው ወታደር ሆዱ ተሸበረበት ፤ጉልበቱም ቄጠማ ሆነበት፡፡ከዚያ ስፍራ ከሬሳ በስተቀር አንድም የሚያውቀው ወታደር ማየት አልቻለም ነበር፡፡

ጦርነቱ እሱ ባለበት በኩል እያደር እየተፋፋመና እየተጋጋለ መጣ፡፡በዚህ ጊዜ መክቶ መቋቋም፤እሩጦም ማምለጥ እንደማይቻል ተገነዘበ፡፡"እንግዲህ ከዚህ በቀር ሌላ ነገር የሚያድነኝ የለም"አለና፤የተደራረቡትን እሬሳዎች ፈነቃቅሎ ገባ፡፡አንዱን እሬሳ በላዩ ላይ ጭኖ ትንፋሹን አሳጥሮ ተኛ፡፡

የወዲያኛውም የወዲህኛውም ወገን በሾተል፤እየተጠማዘዘ፤በፎቄ እየተጓመደ፤እያወካ፤እየተዋጋ፤እየተተራመሰ፤እሱ ወደ ተሸሸገበት በጣም እየቀረበ መጣ፡፡አጠገቡ በደረሰ ጊዜ "የፈረስ አጓዳ ከአሁን አሁን ያደበየኛል"ሲል ሲፈራ ቆይቶ እንደምንም እግሩን ይሰበሰባል፡፡ወዲያው አንድ ተዋጊ ፈረሰኛ አየው፡፡ከፈረሱ ላይ እንደሆነም የዚያን ሳይቆስል የሞተ ሰው እግር በቀጭን ሹል ጦሩ ጠቆም ጠቆም እያደረገ "ይሄስ የሞተ አይመስልም"አለ፡፡በዚህ ጊዜ ያ በውሸት የሞተ ፈሪ ወታደር "አይ!አይ!"እያለና እግሩን እያንፈራገጠ፤ "እሽ ተወኝ ሞቻለሁ"አለ አፉን በእጁ እየተመተመ፡፡

(ዳኛቸው፤የፅሁፍ ጥበብ መመሪያ፤1977፤178-179 ለ9ኛ ክፍል ተሻሽሎ የቀረበ

1፤ ፈሪ ወታደር የተባለው ገፀባህርይ የሚወክለው የወታደር ስነምግባር ምን እንደሆነ ከገለፀው በኃላ ጓደኛው ቢሆን ምን ብላችሁ እንደምትመክሩት ተጠየቃዊ አንድነቱን በጠበቀ አገላለፅ፤በምክንያት በማስረዳት ከአስር ያላነሱ አረፍተነገሮችን የያዘ አንድ አንቀፅ ፃፉ፡፡ (30%)

1.2 ተግባር፤ ሁለት

"በአስራ ስምንተኛው ምዕተ-ዓመት አጋማሽ ገዳማ፤የሱዳን ጦር ምዕራባዊያን የኢትዮጵያን ድንበር እያለፈ ዘረፋ በማካሄድ የአካባቢውን ሕዝብ በጣም ያስቸግራል ነበር፡፡ከዚህም የተነሳ፤የወገን ጦር (የኢትዮጵያ ጦር)ከጎንደር

በመንቀሳቀስ፤በሀገሩ ላይ የተቃጣውን ሕገ ወጥ ድርጊት ለመበቀል ወደ ሰነዓር(በነጭና በጥቁር ዓባይ መካከል በሚገኘው ቦታ)ዘምቶ ተዋግተዋል፡፡ በዚህ ወቅት የሀገራቸውን ክብርና የወገናቸውን ደህንነት ለመስከበር ከዘመቱት ሰዎች ጋር ፈረሶችም ይገኙባቸዋል፡፡

ከጌቶቻቸው ጋር ከዘመቱት ፈረሶች መካከልም ሱቤ ወይም ዞብል በዚህ ዘመቻ ከጌታው ጋር እንዳለ በጠላት እጅ ወደቀ ወይም ማምለጥ ተስኖትም አልነበረም፤ነገር ግን ጌታው ሲማረክ ጌታውን ጥሎ ለመሄድ አልፈለገም፡፡"

"ታዲያ የሱዳን ወታደሮች ሱቤ (ዞቤል)ን ሲያዩ በግዝፈት፤በግርማ ሞገሱና በውበቱ ስለተማረኩ ከሌሎች ምርኮኛ ፈረሶች ነጥለው ለሰነዓር ንጉስ ገፀበረከት አቀረቡለት፡፡በዚህ ጊዜ ንጉሱና የንጉሱ ወታደሮች ዓይኖቻቸውን በዞብል(ሱቤ)ላይ ሰቅለው ውበቱን ማድነቅ ጀመሩ፡፡በተለይ በሱቤ(በዞብል)ውበት የተደነቀው ንጉስ በወቅቱ የአገሩ ጦር ድል ለማድረግ የበቃበትን ሁኔታ ማወደስና የድሉን ደስታ ምክንያት በማድረግ ወታደሮቹን ግብር ማስገባት ነበረበት፡፡ሆኖም በፈረሱ ላይ ባደረበት አድናቆት የተነሳ ማድረግ የሚገባውን ሁሉ ረስቶት ነበር፡፡"ክብረ ስላሴ (1997፤70) ለ9ኛ ክፍል የቀረበ

2 በቀጣዩ አረፍተ ነገር መነሻነት ምንባቡን በአንድ አንቀፅ አሳጥራችው ፃፉ፡፡ (20%)

3 ሱቤ ወይም ዞብል በጠላት የወደቀበት ምክንያት ለምንድ ነው? (20%)

**ለዋናው ጥናት ለቅድመትምህርት የቀረበ የመጻፍ ችሎታን የሚያዳብር ፈተና**

**ትዕዛዝ ሁለት ቀጥሎ ለቀረበው ርዕስ አንድ ገጽ አስረጅ ድርሰት ጻፍ፡፡**

**.አካል ጉዳተኝነት፡፡ (25%)**

.የአካባቢንንጽህናመጠበቅያለውፋይዳ፡፡ **(5%)**

አባሪ ለ የድህረ ፈተና

ለዋናው ጥናት ለድህረ ትምህርት የቀረበ የመጻፍ ፈተና

በወረ ጅሩ ሁለተኛ ትምህርትቤት 9ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ለዋናው ጥናት የቀረበ ድህረ ፈተና

ውድ ተማሪዎች የዚህ ጥያቄ ዋና ዓላማ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን በፅብረቃተኮር መፃፍን ማስተማር የመፃፍ ችሎታን በማሳደግ ረገድ ያለው አስተዋፅኦ በሚል ርዕስ ለሚጠና ጥናት መረጃ ለማግኘት ነው፡፡

እናም የዚህን ጥናት አላማ ማሳካት የሚቻለው እናንተ የምትጠየቁትን ጥያቄ በትክክል መመለስ ስትችሉ ብቻ ነው፡፡ የፈተናው ውጤትም በተመራማሪው ብቻ በሚስጥር ይይዛል፡፡ለምታደርጉት ሙሉ ትብብርም አጥኚው ልባዊ ምስጋና ያቀርባል፡፡

ሀ. ስም አይፃፍም፡፡

ለ.የምትጽፈው(ፊ) ጊዜያዊ የመለያ ኮድ ቁጥሩን ብቻ ነው፡፡

**ትዕዛዝ አንድ ቀጥሎ፡ለቀረበው አንድ አንድ ገጽ አስረጅ ድርሰት ጻፍ፡፡ (100%)**

**ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ርዕሶች በጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታን ለማደበር አንድ አንድ ገጽ በአስረጂ ድርሰት ጻፉ፡፡**

**የግል ንጽህና መጠበቅ ያለው ፋያዳ** (30%)

**የህጻናት መብት** (20%)

**ባህል** (20%)

**የሀገርፍቅር** (15%)

**የጊዜ አጠቃቀም** (15%)

**አባሪ ሐ በቅድመ ፈተና የተመዘገበ ውጤት**

**ሰንጠረዥ** 4.1 **የዋናው ጥናት ቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በቡድኖች**

**ቡድን ሀ**

| | | **አራሚ አንድ** | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **በድን ሀ** | **ይዘት** | **አደረጃጀት** | **ቃላት** | **የቋንቋ አጠቃቀም** | **ስርአተ ጽህፈት** | **ድምር** |
| **የተማሪ ኮድ** | 30% | 20% | 20% | 25% | 5% | 100% |
| 1 | 17 | 13 | 12 | 15 | 3 | 60 |
| 2 | 14 | 10 | 9 | 10 | 2 | 45 |
| 3 | 18 | 11 | 12 | 16 | 3 | 60 |
| 4 | 21 | 16 | 10 | 18 | 5 | 70 |
| 5 | 19 | 13 | 13 | 17 | 3 | 65 |
| 6 | 14 | 12 | 11 | 18 | 5 | 60 |
| 7 | 20 | 13 | 12 | 16 | 2 | 63 |
| 8 | 17 | 11 | 10 | 14 | 4 | 56 |
| 9 | 16 | 11 | 12 | 12 | 3 | 54 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | 15 | 12 | 11 | 10 | 2 | 50 |
| 11 | 17 | 13 | 12 | 15 | 2 | 59 |
| 12 | 17 | 12 | 10 | 17 | 4 | 60 |
| 13 | 16 | 11 | 11 | 13 | 3 | 54 |
| 14 | 18 | 13 | 12 | 15 | 3 | 61 |
| 15 | 16 | 8 | 9 | 12 | 2 | 47 |
| 16 | 13 | 10 | 10 | 11 | 2 | 46 |
| 17 | 17 | 12 | 11 | 14 | 2 | 56 |
| 18 | 16 | 14 | 13 | 14 | 4 | 61 |
| 19 | 16 | 11 | 10 | 15 | 4 | 57 |
| 20 | 21 | 16 | 17 | 20 | 5 | 79 |
| 21 | 18 | 13 | 12 | 19 | 4 | 66 |
| 22 | 13 | 10 | 11 | 12 | 2 | 48 |
| 23 | 16 | 11 | 10 | 12 | 2 | 51 |
| 24 | 19 | 10 | 9 | 17 | 5 | 60 |
| 25 | 16 | 12 | 11 | 13 | 2 | 54 |

| **አራሚ ሁለት** | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቡድን ሀ** | **ይዘት** | **አደረጃጀት** | **ቃላት** | **የቋንቋ አጠቃቀም** | **ስርአተ ጽህፈት** | **ድምር** |
| **የተማሪ ኮድ** | 30% | 20% | 20% | 25% | 5% | 100% |
| 1 | 17 | 12 | 14 | 17 | 5 | 65 |
| 2 | 15 | 10 | 9 | 10 | 2 | 46 |
| 3 | 17 | 12 | 10 | 14 | 3 | 56 |
| 4 | 20 | 16 | 14 | 17 | 3 | 70 |
| 5 | 18 | 13 | 15 | 16 | 3 | 65 |
| 6 | 18 | 14 | 14 | 15 | 4 | 65 |
| 7 | 17 | 10 | 11 | 14 | 3 | 55 |
| 8 | 16 | 12 | 10 | 13 | 3 | 54 |
| 9 | 17 | 11 | 10 | 12 | 2 | 52 |
| 10 | 16 | 11 | 12 | 14 | 3 | 56 |
| 11 | 18 | 14 | 13 | 14 | 3 | 62 |
| 12 | 19 | 12 | 10 | 17 | 5 | 63 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | 15 | 11 | 12 | 14 | 3 | 55 |
| 14 | 18 | 12 | 13 | 16 | 4 | 63 |
| 15 | 14 | 10 | 11 | 11 | 2 | 48 |
| 16 | 15 | 11 | 10 | 13 | 3 | 52 |
| 17 | 17 | 10 | 12 | 15 | 4 | 58 |
| 18 | 18 | 14 | 13 | 15 | 3 | 63 |
| 19 | 16 | 12 | 12 | 14 | 4 | 58 |
| 20 | 20 | 15 | 14 | 16 | 5 | 70 |
| 21 | 20 | 13 | 13 | 15 | 2 | 63 |
| 22 | 15 | 11 | 10 | 12 | 2 | 50 |
| 23 | 14 | 10 | 10 | 12 | 2 | 48 |
| 24 | 15 | 12 | 10 | 14 | 3 | 54 |
| 25 | 16 | 11 | 13 | 14 | 4 | 58 |

**የዋናው ጥናት ቅድመ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በቡድኖች ቡድን ለ**

| አራሚ አንድ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቡድን ለ** | **ይዘት** | **አደረጃጀት** | **ቃላት** | **የቋንቋ አጠቃቀም** | **ስርአተ ጽህፈት** | **ድምር** |
| **የተማሪ ኮድ** | 30% | 20% | 20% | 25% | 5% | 100% |
| 1 | 17 | 12 | 10 | 15 | 4 | 58 |
| 2 | 14 | 10 | 11 | 12 | 2 | 49 |
| 3 | 22 | 11 | 10 | 17 | 2 | 62 |
| 4 | 19 | 10 | 12 | 13 | 3 | 57 |
| 5 | 17 | 12 | 10 | 14 | 2 | 55 |
| 6 | 19 | 13 | 15 | 16 | 4 | 67 |
| 7 | 18 | 11 | 10 | 13 | 2 | 54 |
| 8 | 19 | 12 | 12 | 14 | 2 | 59 |
| 9 | 18 | 13 | 11 | 15 | 3 | 60 |
| 10 | 18 | 14 | 12 | 14 | 2 | 60 |
| 11 | 17 | 11 | 13 | 15 | 4 | 60 |
| 12 | 17 | 13 | 12 | 13 | 2 | 57 |
| 13 | 20 | 14 | 16 | 14 | 2 | 66 |
| 14 | 17 | 11 | 12 | 15 | 2 | 57 |
| 15 | 17 | 11 | 12 | 16 | 4 | 60 |
| 16 | 18 | 14 | 12 | 12 | 3 | 59 |
| 17 | 19 | 11 | 13 | 16 | 3 | 62 |
| 18 | 15 | 10 | 11 | 13 | 2 | 51 |
| 19 | 14 | 10 | 10 | 11 | 2 | 47 |
| 20 | 17 | 12 | 14 | 15 | 4 | 62 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | 20 | 10 | 11 | 13 | 2 | 56 |
| 22 | 18 | 12 | 13 | 14 | 2 | 59 |
| 23 | 17 | 11 | 10 | 12 | 2 | 52 |
| 24 | 16 | 10 | 11 | 13 | 3 | 53 |
| 25 | 18 | 13 | 12 | 14 | 4 | 61 |

| | አራሚ ሁለት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን ለ | ይዘት | አደረጃጀት | ቃላት | የቋንቋ አጠቃቀም | ስርዓተ ጽህፈት | ድምር |
| የተማሪ ኮድ | 30% | 20% | 20% | 25% | 5% | 100% |
| 1 | 17 | 13 | 11 | 15 | 4 | 60 |
| 2 | 18 | 10 | 11 | 12 | 2 | 53 |
| 3 | 20 | 13 | 13 | 14 | 4 | 64 |
| 4 | 14 | 11 | 13 | 13 | 2 | 53 |
| 5 | 18 | 13 | 12 | 14 | 3 | 60 |
| 6 | 17 | 11 | 11 | 14 | 3 | 56 |
| 7 | 15 | 12 | 10 | 14 | 2 | 53 |
| 8 | 18 | 10 | 12 | 11 | 2 | 53 |
| 9 | 17 | 13 | 12 | 13 | 3 | 58 |
| 10 | 15 | 13 | 11 | 13 | 2 | 54 |
| 11 | 18 | 12 | 14 | 16 | 4 | 64 |
| 12 | 17 | 11 | 10 | 12 | 4 | 54 |
| 13 | 18 | 16 | 15 | 17 | 3 | 69 |
| 14 | 16 | 12 | 10 | 14 | 3 | 55 |
| 15 | 18 | 11 | 13 | 14 | 2 | 58 |
| 16 | 16 | 12 | 12 | 13 | 3 | 56 |
| 17 | 19 | 13 | 11 | 16 | 5 | 64 |
| 18 | 16 | 12 | 12 | 14 | 2 | 56 |
| 19 | 14 | 11 | 10 | 12 | 2 | 49 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | 17 | 12 | 13 | 16 | 2 | 60 |
| 21 | 22 | 13 | 11 | 11 | 3 | 60 |
| 22 | 18 | 11 | 12 | 17 | 4 | 62 |
| 23 | 17 | 10 | 11 | 14 | 3 | 55 |
| 24 | 18 | 12 | 13 | 16 | 4 | 63 |
| 25 | 17 | 15 | 13 | 15 | 2 | 62 |

አባሪ መ በድህረ ፈተና የተመዘገበ ውጤት

የዋናው ጥናት የድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በቡድኖች ቡድን ሀ

| አራሚ አንድ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በድን ሀ | ይዘት | አደረጃጀት | ቃላት | የቋንቋ አጠቃቀም | ስርአተ ጽህፈት | ድምር |
| የተማሪ ኮድ | 30% | 20% | 20% | 25% | 5% | 100% |
| 1 | 20 | 15 | 16 | 18 | 5 | 74 |
| 2 | 20 | 14 | 15 | 16 | 3 | 68 |
| 3 | 19 | 13 | 13 | 15 | 3 | 63 |
| 4 | 18 | 14 | 15 | 16 | 3 | 66 |
| 5 | 15 | 10 | 11 | 12 | 2 | 50 |
| 6 | 18 | 14 | 14 | 13 | 3 | 62 |
| 7 | 16 | 11 | 12 | 13 | 3 | 55 |
| 8 | 19 | 10 | 13 | 13 | 2 | 57 |
| 9 | 22 | 17 | 15 | 18 | 5 | 77 |
| 10 | 20 | 14 | 15 | 17 | 4 | 70 |
| 11 | 17 | 13 | 12 | 14 | 2 | 58 |
| 12 | 18 | 12 | 13 | 15 | 2 | 60 |
| 13 | 16 | 11 | 10 | 13 | 2 | 54 |
| 14 | 17 | 13 | 14 | 17 | 3 | 64 |
| 15 | 16 | 8 | 9 | 12 | 2 | 54 |
| 16 | 13 | 10 | 10 | 11 | 2 | 47 |
| 17 | 17 | 12 | 11 | 14 | 2 | 53 |
| 18 | 16 | 14 | 13 | 14 | 4 | 56 |
| 19 | 16 | 11 | 10 | 15 | 4 | 57 |
| 20 | 21 | 16 | 17 | 20 | 5 | 79 |
| 21 | 18 | 13 | 12 | 19 | 4 | 66 |
| 22 | 13 | 10 | 11 | 12 | 2 | 48 |
| 23 | 16 | 11 | 10 | 12 | 2 | 51 |
| 24 | 17 | 10 | 12 | 13 | 3 | 55 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 25 | 16 | 9 | 10 | 12 | 2 | 49 |

| አራሚ ሁለት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን ሀ | ይዘት | አደረጃጀት | ቃላት | የቋንቋ አጠቃቀም | ስርአተ ጽህፈት | ድምር |
| የተማሪ ኮድ | 30% | 20% | 20% | 25% | 5% | 100% |
| 1 | 21 | 14 | 15 | 16 | 4 | 70 |
| 2 | 20 | 15 | 17 | 18 | 5 | 75 |
| 3 | 19 | 15 | 13 | 17 | 3 | 67 |
| 4 | 20 | 16 | 17 | 19 | 5 | 77 |
| 5 | 12 | 10 | 11 | 10 | 2 | 45 |
| 6 | 18 | 14 | 14 | 15 | 4 | 65 |
| 7 | 17 | 10 | 11 | 14 | 3 | 55 |
| 8 | 16 | 12 | 10 | 13 | 3 | 54 |
| 9 | 17 | 11 | 10 | 12 | 2 | 52 |
| 10 | 16 | 11 | 12 | 14 | 3 | 56 |
| 11 | 18 | 14 | 13 | 14 | 3 | 62 |
| 12 | 19 | 12 | 10 | 17 | 5 | 63 |
| 13 | 15 | 11 | 12 | 14 | 3 | 55 |
| 14 | 18 | 12 | 13 | 16 | 4 | 63 |
| 15 | 14 | 10 | 11 | 11 | 2 | 48 |
| 16 | 15 | 11 | 10 | 13 | 3 | 52 |
| 17 | 17 | 10 | 12 | 15 | 4 | 58 |
| 18 | 18 | 14 | 13 | 15 | 3 | 63 |
| 19 | 16 | 12 | 12 | 14 | 4 | 58 |
| 20 | 20 | 15 | 14 | 16 | 5 | 70 |
| 21 | 20 | 13 | 13 | 15 | 2 | 57 |
| 22 | 15 | 11 | 10 | 12 | 2 | 51 |
| 23 | 13 | 10 | 10 | 13 | 3 | 49 |
| 24 | 13 | 12 | 10 | 10 | 3 | 48 |
| 25 | 16 | 11 | 13 | 13 | 3 | 56 |

የዋናው ጥናት ድህረ ትምህርት ጽብረቃተኮር መጻፍ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በቡድኖች ቡድን ለ

| አራሚ አንድ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን ለ | ይዘት | አደረጃጀት | ቃላት | የቋንቋ አጠቃቀም | ስርአተ ጽህፈት | ድምር |
| የተማሪ ኮድ | 30% | 20% | 20% | 25% | 5% | 100% |
| 1 | 15 | 14 | 12 | 15 | 3 | 59 |
| 2 | 18 | 11 | 12 | 15 | 2 | 58 |
| 3 | 19 | 14 | 14 | 13 | 3 | 65 |
| 4 | 19 | 10 | 12 | 13 | 3 | 57 |
| 5 | 17 | 12 | 10 | 14 | 2 | 55 |
| 6 | 19 | 13 | 15 | 16 | 4 | 67 |
| 7 | 18 | 11 | 10 | 13 | 2 | 54 |
| 8 | 19 | 12 | 12 | 14 | 2 | 59 |
| 9 | 18 | 13 | 11 | 15 | 3 | 60 |
| 10 | 18 | 14 | 12 | 14 | 2 | 60 |
| 11 | 17 | 11 | 13 | 15 | 4 | 60 |
| 12 | 17 | 13 | 12 | 13 | 2 | 57 |
| 13 | 20 | 14 | 16 | 14 | 2 | 66 |
| 14 | 17 | 11 | 12 | 15 | 2 | 57 |
| 15 | 17 | 11 | 12 | 16 | 4 | 60 |
| 16 | 18 | 14 | 12 | 12 | 3 | 59 |
| 17 | 19 | 11 | 13 | 16 | 3 | 62 |
| 18 | 15 | 10 | 11 | 13 | 2 | 51 |
| 19 | 14 | 10 | 10 | 11 | 2 | 47 |
| 20 | 17 | 12 | 14 | 15 | 4 | 62 |
| 21 | 20 | 10 | 11 | 13 | 2 | 56 |
| 22 | 18 | 12 | 13 | 14 | 2 | 59 |
| 23 | 17 | 11 | 10 | 12 | 2 | 52 |
| 24 | 18 | 10 | 11 | 13 | 3 | 55 |
| 25 | 17 | 12 | 12 | 14 | 4 | 59 |

| አራሚ ሁለት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን ለ | ይዘት | አደረጃጀት | ቃላት | የቋንቋ | ስርዓተ | ድምር |

| | | | | አጠቃቀም | ጽህፈት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **የተማሪ ኮድ** | 30% | 20% | 20% | 25% | 5% | 100% |
| 1 | 17 | 11 | 12 | 14 | 3 | 57 |
| 2 | 17 | 11 | 9 | 11 | 2 | 50 |
| 3 | 16 | 13 | 11 | 18 | 5 | 63 |
| 4 | 14 | 11 | 13 | 13 | 2 | 53 |
| 5 | 18 | 13 | 12 | 14 | 3 | 60 |
| 6 | 17 | 11 | 11 | 14 | 3 | 56 |
| 7 | 15 | 12 | 10 | 14 | 2 | 53 |
| 8 | 18 | 10 | 12 | 11 | 2 | 53 |
| 9 | 17 | 13 | 12 | 13 | 3 | 58 |
| 10 | 15 | 13 | 11 | 13 | 2 | 54 |
| 11 | 18 | 12 | 14 | 16 | 4 | 64 |
| 12 | 17 | 11 | 10 | 12 | 4 | 54 |
| 13 | 18 | 16 | 15 | 17 | 3 | 69 |
| 14 | 16 | 12 | 10 | 14 | 3 | 55 |
| 15 | 18 | 11 | 13 | 14 | 2 | 58 |
| 16 | 16 | 12 | 12 | 13 | 3 | 56 |
| 17 | 19 | 13 | 11 | 16 | 5 | 64 |
| 18 | 16 | 12 | 12 | 14 | 2 | 56 |
| 19 | 14 | 11 | 10 | 12 | 2 | 49 |
| 20 | 17 | 12 | 13 | 16 | 2 | 60 |
| 21 | 22 | 13 | 11 | 11 | 3 | 60 |
| 22 | 18 | 11 | 12 | 17 | 4 | 62 |
| 23 | 17 | 10 | 11 | 14 | 3 | 56 |
| 24 | 18 | 12 | 13 | 16 | 4 | 57 |
| 25 | 17 | 11 | 13 | 15 | 2 | 58 |